ምስጢራተ ቤተክርስቲያን

መግቢያ

<u>አዘጋጅ</u>

ሊቀ ጉባኤ አባ አበራ በቀለ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

የሰበካ ጉባኤ ማደራጃ መምሪያ ኃላፊ

<u>አሳታሚ</u>

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ

ማኅበረ ቅዱሳን

አዲስ አበባ

1996 **ዓ.ም**

www.eotc-mkidusan.org

© ማኅበረ ቅዱሳን
1996 ዓ.ም.

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

ይህ መጽሐፍ
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
በማኅበረ ቅዱሳን
የኢዲቶሪያል ቦርድ ታርሞና ተስተካክሎ
የተፈቀደ ነው::

አድራሻ

በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ
በሰ/ት/ቤቶች ማ/ሠምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን፣ ኅትመት ዝግጅት ማስተባበሪያ ክፍል

ፖ.ሳ.ቁ. 80078
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ስልክ 55 63 28/27

Email- eoc-m-kidusan@telecom.net.et

www.eotc-mkidusan.org



«አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነስቷልና። ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ በክርስቶስ ደግሞ ሀያዋን ይሆናሉና።»1ኛቆሮ.15.20-21



«እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤ ብርቱ የሆነ በእርሱ ለእኔ ታላቅ ሥራን አድርጓልና።» ሉቃ. 1.49

መታሰቢያ ነቲ



«በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ወጣቱን ትውልድ ለአንድ ዓላማ በማሰለፍና በሃይማኖታዊ አኗኗር በመቅረጽ የብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕን ያህል የተሳካለት ሰው ያለ አይመስልም። ከዕስተ ዕረፍታቸው 10 ዓመታት በኋላ አንኳን የጻፏቸው መጻሕፍት፣ ያዘጋጇቸው የጽሑፍ ስብከቶችና በቃል ያስተላለፏቸው ትምህርቶች ለአያሌ ሰንበት ት/ቤቶች፣ የካህናትና የመምህራን ማሠልጠኛዎች ማስተማርያና የተግባር መመሪያ ሆነዋል።»

ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ፣ ነሐሴ 1994 ዓ.ም.

ይህ መጽሐፍ ወጣቱን ትውልድ በነገረ ሃይማኖት ዕውቀትና በመንፈሳዊ ሕይወት ለመቅረጽ፣ ትውልዱ የቤተ ክርስቲያን ፍቅር አንዲኖረው ለማድረግ ለተጉት፣ ዛሬ ላለው ኦርቶዶክሳዊ የስብከት ዘዴ ፋና ወጊ ለሆኑት፣ ዘመኑን የሚዋጁ የትምህርተ ሃይማኖትና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ መጻሕፍትን ላዘጋጁት፣ ቤተ ክርስቲያን በዓለም መድረክ ተገቢ ቦታዋን እንድታገኝ ለተጋደሉት፣ የዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳምና የካህናት ማሠልጠኛ መሥራች ለሆኑት፣ ለ21ኛው መ/ክ/ዘ «ከሣቴ ብርሃን» ለብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ (1932-1982 ዓ.ም.) መታሰቢያ ይሁን።

ጸሎታቸውና በረከታቸው በሁላችን ላይ ይደር፣ አሜን።

www.eotc-mkidusan.org

መግቢያ

«የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ» 2ኛጢሞ.3÷14 ከሚባሉት ውስጥ መጻሕፍተ ሊቃውንት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ሊቃውንት በየዘመናቸው የዘመኑን ጥያቄ ሊመልሱ የሚችሉ መጻሕፍትን አዘጋጅተዋል፡፡ በተለይም ከመናፍቃን መነሣት በኋላ ያሉት በየዘመናቸው ለተነሡት ጥያቄዎች ሁሉ መልስ የሚሆኑና የምእመናን ልቡና በኑፋቄ ማዕበል እንዳይናወጽ የሚያደርጉትን ምሥጢራት በፈርጅ እየተነተኑ ጽፈዋል፡፡ እነዚህም እንደ አምስቱ አዕማደ ምሥጢራት፣ ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን፣ ነገረ ማርያምና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

እነዚህን መጻሕፍት ሲጽፉ ወይንም ምሥጢራት እያሉ ሲያዘጋጁም ከራሳቸው አንቅተው አይደለም፡፡ መሠረቱ የጌታችንና እርሱ አድሮባቸው ቀድመው ትንቢት የተናገሩ የነቢያት በኋላም ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው የተረጐሙና ያስተማሩ የሐዋርያት ትምህርት ነው፡፡ ከዚህ ውጭ አልተንቀሳቀሱም፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ «መሠረትን ደግመን አንመሥርት÷ እርሱም ከሞተ ሥራ ንስሐና በእግዚአብሔር እምነት÷ ስለ ጥምቀቶችና እጆችንም ስለመጫን ስለ ሙታንም ትንሣኤ ስለ ዘላለም ፍርድም ትምህርት ነው፡፡» ዕብ.6÷2-3 ያለውን ምክር የሚዘነጉት አይደሉምና፡፡

ሠለስቱ ምእት በጉባኤ ኒቅያ የደነገጉት የሃይማኖት መግለጫ ዶግማ ይህን መሠረት ያደረገ ነበር፡፡ ጉባኤ ኤፌሶንም በቀደሙት ሁለት ጉባኤያት የተረቀቁት አናቅጽ ላይ እንዳይጨመር እንዳይቀነስ በሚል አጸናው፡፡ ከዚህ በኋላ ሊቃውንት እነዚህን ድንጋጌዎች መሠረት አድርገው እያብራሩ እያስፋፉ በመጻፍ ምእመናንን በትምህርት አንጸዋል፣ ለሰማዕትነትም አብቅተዋል፡፡ በቀደመው መሠረት ላይ የታነፀ እውነተኛ ሕንፃም ይህ ነው፡፡ ከዚህ የወጣው ግን በእሳት በሚፈተንበት ጊዜ ገለባነቱ በመቃጠል ይገለጣል፡፡ 1ኛቆሮ.3÷10-15፡፡

«ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት» በሚል ርእስ የተዘጋጀው ይህ መጽሐፍም በመጀመሪያ የሚተነትነው በሦስቱ ጉባኤያት ላይ የተደነገጉትን አሥራ ሁለቱን አናቅጸ ሃይማኖት ነው፡፡ ከዚህም በኋላ ሕግጋትን /ሕገ ልቡናን፣ ሕገ ኦሪትንና ሕገ ወንጌልን/ እያዋሐደና እያመሰጠረ «እኔ ክርስቶስን እንድመስል እናንተም እኔን ምሰሉ፡፡» 1ኛቆሮ.11÷1 በማለት ቅዱስ ጳውሎስ የሰበከለትን የሁላችንም መሪ ፈታውራሪ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንድንመስል ክርስቲያናዊ ሕይወትን በሰፊው ይተነትናል፣ ይልቁንም «ከሁሉም የሚበልጥ» የተባለውን «ሕገ ተፋቅሮን» በአጽንኦት ይገልጣል፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ የእነዚህን ዓይነት መጻሕፍትን አጠቃላይ ጠቃሚታ የተናገረው በሁለት ከፍሎ ነበር፡፡ የመጀመሪያውን «... ኢየሱስን በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብና ትምህርት የሚሰጡ» በማለት በሃይማኖት የምን ጸናባቸው መሆናቸውን ከገለጠ በኋላ ሁለተኛውን ደግሞ «የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፣ ... ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር» በማለት ለክርስቲያናዊ ሕይወታችን ያላቸውን አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ዘርዝሮ አስቀምጠልናል፡፡ 2ኛጢሞ.3÷14-17፡፡

ይህ መጽሐፍም ከጥንቶቹ ሊቃውንት፣ በመካከለኛው ዘመንና በአሁኑ ዘመን ያሉትንም ሊቃውንት ትርጓሜና ትምህርት እንደ አበባ ቀስሞ እንደ ማር አጣፍጦ የሚያቀርብ የሃይማኖት ድንጋጌን /ዶግማን/ በስፋትና በጥልቀት የሚተነትን ምግባረ ወንጌልንም የሚያስተምር በመሆኑ ለሊቃውንቱ ለበለጠ የምርምርና የጽሑፍ ሥራ በምንጭነት፣ ለመምህራን በማጣቀሻነት፣ ለሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች ደግሞ በቋሚ መረጃነት የሚያገለግል ጥልቅ መጽሐፍ ነው፡፡ ይልቁንም መጽሐፉ የመጀመሪያው ረቂቅ ከተሠራ በኋላ እየታሸና እየተመሣጠረ በዝግጅት ብቻ ከአሥር ዓመታት በላይ የፈጀ፣ በእነዚህ ዓመታት ብዙ ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እየተመለከቱ አስተያየት የሰጡበት፣ ወጣት ሰባክያንም ጥያቄዎቻቸውንና አሳባቸውን በመሰንዘር በየጊዜው በምሥጢር እንዲጐለምስና በይዘት እንዲያድግ ያደረጉት ስለሆነ ጠቀሜታው በዚህ አጭር መግቢያ ከሚገለጸው በላይ ነው፡፡ ከመጽሐፉ መደበኛ ይዘት (text) በተጨማሪ ከመቶ በላይ ጥልቅና ምሥጢራዊ የሆኑ የግርጌ ማስታዎሻዎችን (foot notes) የያዘው ይህ መጽሐፍ ቤተ ክርስቲያናችን እስካሁን የምታስተምረውን ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት በስፋትና በጥልቀት በአንድ ይዘት በማቅረብ የመጀመሪያው ይመስላል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ በመምህራን፣ በካህናትና በምእመናን እጅ ብቻ ሳይሆን በእያንዳንዱ ሰው እጅ ሊቀመጥ ይገባል፡፡

በመጨረሻም የመጽሐፍ ዝግጅቱ በወሰዳቸው ጥቂት በማይባሉት በእነዚህ ዓመታት የእግዚአብሔር ረዳትነትና ተአምር በግልጽ ታይቷል፡፡ ስለዚህም አስቀድመን በኋሊና ለመታሰቡ በአንደበት ለመነገሩ ስመ ባሕርዩ የእግዚአብሔር አምላካችን፣ ስመ ሥጋዌው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ከፍ ከፍ ይበል ይክበር ይመስገን እንላለን፡፡ በመቀጠልም በእርሱ ፈቃድ በረዳትነቱም በእነዚህ ዓመታት ውስጥ መጽሐፉን ያለመሰልቸት እየተመለከቱ አስተያየታቸውን ለሰጡት ሊቃውንት ሁሉ ይልቁንም ደግሞ በእነዚህ ሁለት የመጨረሻ ዓመታት በተለያዩ ጊዜያት በፍጹም ልባዊ ፈቃድና በእውነተኛው የክርስትና ፍቅር ተይዘው በማረምና አስተያየታቸውን በመስጠት እንዲሁም አድካሚውን የጽሕፈት፣ የለቀማና የቅርጽ (formatting) ሥራ የሠሩትን ማንኛውንም ድጋፍና ምክር የለገሡትን ሁሉ በእግዚአብሔር ስም እናመሰግናለን፡፡

የኅትመት ዝግጅት ማስተባበሪያ ክፍል

ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotc-mkidusan.org

የአርእስት ማውጫ

ርእስ **ገጽ**

ክፍሉ ሁለት

የክርስቶስ የማዳን ሥራና ጸጋው
በቃሉና በምስጢራተ ቤተክርስቲያን

መግቢያ 222

ምዕራፍ አንድ
ስለመዳናችን ምስጢር፣ ስለጸጋና
ስለቤተክርስቲያን ምስጢራት

ሀ. መዳናችን ቃሉን በማመንና ምስጢራትን በመፈጸም ነው 224
1. **ቃለ እግዚአብሔር፣ ጸሎትና ምስጢራት አይለያዩም** 224
2. **ለመዳናችን ጥምቀትን እንድንፈጽም ታዟል** 225
3. **የዕለተ ዓርቡ የማዳን ሥራ በሥጋውና በደሙ** 226

ለ. ስለ ጸጋና ምስጢራተ ቤተክርስቲያን 234
1. **የጸጋ ትርጉም- ምንነቱና ዓይነቱ** 234
2. **ጸጋው ከኃጢአትና በሕግም ከመኮነን ያድነናል** 237
3. **የጸጋና የምስጢራተ ቤተክርስቲያን ግንኙነት** 240

ክፍል ሁለት

የክርስቶስ የማዳን ሥራና ጸጋው በቃሉና በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን

መ ግ ቢ ያ

የክፍል ሁለት ርእስ እንደዚህ በረጅሙ የተቀረጸበት ምክንያት የጽሑፉን ዐቢይ መልእክት በቅድሚያ ለማስገንዘብ ያህል ነው። ባጭሩ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን በሚል ርእስ ተነሥቶ ስለ እያንዳንዱ ምሥጢራት ታሪክና የአፈጻጸም ሥርዓት፥ ከሌላውም አብይተ ክርስቲያናት ጋር ያለውን ግን ኙነትና ልዩነት በማነፃፀር መግለጡ በበቃ ነበር። ነገር ግን ስለዚህ ጉዳይ በየጊዜው በአገራችን ምሁራን የተዘጋጁ ብዙ ጠቃሚ መጻሕፍት ስላሉ እነዚህኑ ማጥናት እንጂ እነርሱን አስመስሎ እንደገና መጻፉ እምብዛም ተፈላጊነት አይ ኖረውም። በተለይም በሊቃውንት ጉባኤ ተዘጋጅቶ በ1988 ዓ.ም. ለሁለተኛ ጊዜ የታተመው <u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት፥ ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት</u> እንደዚሁም በማኅበረ ቅዱሳን አዘጋጅነት በ1993 ዓ.ም. የታተመው <u>ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት</u> የተባሉ መጻሕፍት ከላይ ለተጠቀሱት ጉዳዮች ጠቃሚነታቸው ስለታወቀ ለመማሪያም ሆነ ለማስተማሪያ ያስፈልጉናል።

በነዚህና በመሳሰሉት መጻሕፍት ላይ አዲስ የሚጨመር ነገር ኖሮ ሳይ ሆን ይኸንኑ ትምህርትና እምነት ለአዲሱ ትውልድ ጥያቄ እንደሚስማማ አድ ርጎና ያንኑ በበለጠ አጠናክሮ ለማቅረብ ታስቦ የተጻፈ ነው። ይልቁንም ስለ ምሥጢራት አስፈላጊነት በአዲሱ ትውልድ ዘንድ እየተረሳ እንዳይሄድ ለማድረግና በጊዜያችንም እየጐላና እየገፋ ለመጣው ለተቃዋሚዎች ጥያቄ ምላሽ መስጠት ግዴታ ሆኖብናል። ስለዚህም በጽሑፋችን ትኩረት የምንሰጠውና በአ ጽንኦት የምናጠናው ዐቢይ ጉዳይ በክርስቶስ የመዳናችን ምሥጢርና በቤተ ክርስቲያናችንም የምሥጢሩ አፈጻጸም በምን ሁኔታና ሥርዓት እንደሆ ነ በመመልከት ነው።

አንዳንድ ወገኖች የመዳናችን ምሥጢር በእምነት ብቻ ስለሚፈጸም ሌላ ነገር አያስፈልግም ይላሉ። ቃለ እግዚአብሔርን ሰምቶ በማመን ብቻ መጽደቅ ስለሚቻል የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊነት አይታየንም በማለት አጥ ብቀው ይከራከራሉ። ነገር ግን እነርሱ እንደሚሉት ሳይሆን መዳናችን ቃለ እግዚአብሔርን ሰምቶ በማመን፥ ቃሉን ሰምቶ በማድረግና ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን በመፈጸም እንደሆነ ቅዱሳት መጻሕፍትን ምስክር በማድረግ በአ ጭሩ ለማስረዳት ሞክረናል።

ከትእዛዛት አንዱን የሻረ ሁሉን እንደ ሻረ ስለሚቆጠር ሁሉንም መፈጸም ይገባናል እንጂ አንዱን ብቻ መርጦ መያዝ ሌላውን ማጣጣል ሁሉን ም እንዳፈረሰ ይቆጠራል (ያዕ.2፥10)። እርሱ የደኅንነታችንና የጽድቃችን ሁሉ ባለቤት ክርስቶስ ሁሉንም እንድንፈጽም አዞናል። ጌታ "ያመነ የተጠመቀ ይድናል" ነው ያለው እንጂ ያመነ ብቻ አላለም (ማር.16፥16)። ከውኃና ከመንፈስ ያልተወለደ መንግሥተ ሰማያት እንደማይገባ ጌታ አረጋግጧል (ዮሐ.3፥5)። ጥምቀት የምሥጢራት ሁሉ መጀመሪያ ነው። ጌታም የጥምቀትን ምሥጢር ለማጠናከር እርሱ ራሱ አርአያ ሊሆነን ከሁሉ በፊት ሥራውን የጀመረው ራሱን ዝቅ አድርጎ በእደ ዮሐንስ በመጠመቅ ነበር። እርሱ እንደ

www.eotc-mkidusan.org

ተጠመቀ እኛም እንድንጠመቅ አዘዘን፡፡ እንግዲህ ጌታ ያዘዘውን የጥምቀትን ሥርዓት በጌታ ቃል ተመርኩዘን እንፈጽመዋለን፡፡ ጌታ በቃሉ ያዘዘውን በተግባር የፈጸመውን መሠረት በማድረግ ስለ ሌሎቹ ምሥጢራትም በየቦታቸው ገልጸናል፡፡

የእግዚአብሔር የማዳን ሥራው በዕለተ ዓርብ አንድ ጊዜ የተፈጸመ ሲሆን የመዳኑ ጸጋ በየጊዜው ለሚነሡት ትውልድ ሁሉ የሚደርሰው በቃሉ አ ገልግሎት ማለት በሰብኩተ ወንጌልና ምሥጢራትን በመፈጸም ነው፡፡ ስለዚህ ነው ሐዋርያት "ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን" የሚሉት (የሐዋ.6፡4)፡፡ ቃሉን ማገልገል ማለት የጌታን ቃል ማስተማር "በስሙም ን ስሐና የኃጢአት ሥርየት" መሰበክን ያመለክታል (ሉቃ.24፡47)፡፡ በጸሎት መትጋትም ማለት በክርስቶስ ስም አምነው ንስሐ ለሚገቡትና የኃጢአት ሥርየት ለሚያስፈልጋቸው ተገቢውን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን በልዩ ልዩ ሥርዓተ ጸሎት አማካይነት መፈጸም እንደሆነ ከሐዋርያት የዕለት በዕለት ተግባር ለማወቅ ይቻላል፡፡ የመጀመሪያዎቹ አማኞች ቃሉን በማመንና በመቀበል ብቻ አልቀሩም፡፡ በሐዋርያት ሥራ እንደ ተጻፈው "ቃሉንም የተቀበሉት ተጠመቁ፥ በዚያም ቀን ሦስት ሺህ የሚያህል ነፍስ ተጨመሩ፤" ካለ በኋላ "በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቁረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር" ይላል (የሐዋ.ሥራ 2፡41-42)፡፡ እንግዲህ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች የሐዋርያትን ትምህርት በመስማት ቃሉንም በማመን ምሥጢራትንም በመፈጸም "በየጸሎቱም" በመትጋት በመንፈሳዊ ፍቅርና አንድነት መኖራቸውን እያስታወስን የእነርሱን አርአያ መከተል ክርስቲያናዊ ግዴታችን መሆኑን አ መልክተናል፡፡

በዚህ ጽሑፍ ላይ በተለይም በክፍል ሁለት በምዕራፍ አንድ ለማስረዳት የሞከርነው ከላይ የጠቀስነውን የመጀመሪያዋን ቤተ ክርስቲያን ፈለግ በመከተል የመዳናችን ጸጋ ለሁላችን የሚደርሰን በቃሉ በማመንና ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን በመፈጸም እንደሆነ ነው፡፡ ምክንያቱም ቃለ እግዚአብሔርና ምሥ ጢራተ ቤተ ክርስቲያን ለመዳናችንና ለመቀደሳችን ሲባል ከአንድ ጌታ የተሰጡ ናቸውና፡፡ ስለዚህ ነው ገና ከመጀመሪያው በርእሱ ላይ ሳይቀር የመዳናችን ሥራና ጸጋ በቃሉና በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነ የገለጽነው፡፡

ስለ ሰባቱ ምሥጢራት እያንዳንዱን ከመግለጻችን በፊት የጸጋን ትርጉምና ዓይነት እንዲሁም ጸጋ ከኃጢአትና ከሕግ በተለይም ከቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት ጋር ያለውን ግንኙነት በአጭሩ ለማስረዳት ሞክረናል፡፡ ይህም የሆ ነበት ምክንያት ከእያንዳንዱ ምሥጢራት ስለምናገኘው የጸጋ ዓይነት በቅድሚያ እንድናውቅና አስፈላጊው ግንዛቤ እንዲኖረን ለማድረግ ነው፡፡

በክፍል አንድ ምዕራፍ ሦስት "የመዳናችንና የመቀደሳችን ምሥጢር" ፡ የጸጋው አሰጣጥና የሥራው አፈጻጸም በመንፈስ ቅዱስና በቤተ ክርስቲያን አማካይነት እንዴት እንደሚከናወን በአጭሩ ገልጸናል፡፡ በተለይም በጸሎተ ሃይማኖት አንቀጽ ፮፣ ፊደል ተራ (ሐ) ጋር የዚህ ክፍል ሁለት አርእ ስተ ትምህርት ቀጥታ የተያያዘ ነው፡፡ እንደዚሁም በአንቀጽ ፲ "ኃጢአት በሚሠረይባት በአንዲት ጥምቀት እናምናለን" ከሚለው ኃይለ ቃል በከፊል በመውሰድ "ስለ ሥርየተ ኃጢአት" ብቻ አስረድተን የቀረውን ማለት "ጥምቀትን" በተመለከተ ግን ከምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ጋር እንደምንገልጽ በዚያው በቦታው ላይ አመልክተናል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ጥምቀት፥ የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንዱና የመጀመሪያው ስለሆነ ነው፡፡

እንግዲህ በዚህ ክፍል፥ በመጀመሪያ የጌታችንን የማዳን ሥራውንና ጸጋውን በእግዚአብሔር የተጠሩት ሁሉ በቃሉ አገልግሎት፥ በቤተ ክርስቲያን ጸሎትና በተቀደሱት ምሥጢራት አማካይነት እንዴት እንደሚያገኙት በአጠቃላይ መልኩ እንመለከታለን፡፡ ቀጥሎም ከቃለ እግዚአብሔር ጋር ከሰባቱ ምሥጢራት ሁሉ በአንድነትና በተናጠል ከእያንዳንዳቸው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ለምእመናን ስለሚታደለው ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎች ለማስረዳት እንሞክራለን፡፡

www.eotc-mkidusan.org

ምዕራፍ አንድ

ስለመዳናችን ምሥጢር፥ ስለ ጸጋና ስለቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት

ሀ) መዳናችን ቃሉን በማመንና ምሥጢራትን በመፈጸም ነው

1. ቃለ እግዚአብሔር፥ ጸሎትና ምሥጢራት አይለያዩም

በክፍል አንድ ጸሎተ ሃይማኖትን መሠረት በማድረግ ስለ ክርስትና እምነት በመጠኑ ተምረናል። ይህ የእምነት ትምህርትና እውቀት፥ ጸጋና በረከት ሁሉ ቃለ እግዚአብሔርን በመስማት ብቻ ስለሚገኝ ለመዳናችን የቃሉ አገልግሎት ማለት ስብከተ ወንጌል ብቻ እንጂ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ለምን ያስፈልጋሉ? በማለት የሚጠይቁ ወገኖች ይኖራሉ። እርግጥ ነው ከሁሉ በፊት ለመዳናችን እምነት ያስፈልጋል። እምነት ደግሞ ከመስማት ይመጣል፤ መስማት ደግሞ ከእግዚአብሔር ቃል ነው ማለት በስብከተ ወንጌል ነው (ሮሜ.10፥17)። ነገር ግን መዳናችን የወንጌልን ቃል በመስማት ይጀምራል እንጂ በዚህ አያከትምም። ይህ በመጀመሪያ ደረጃ የሚሰጥ ላላመኑት ሁሉ፥ ለፍጥረት ሁሉ የሚሰበክ የወንጌለ መንግሥት ጥሪ፥ የንስሐ ጥሪ ወደ ክርስቶስና ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ማቅረቢያ ነው። በዚህም የመጀመሪያ ሥራ እግዚአብሔር የመረጣቸውን ሁሉ በሀብት ስቦ በረድኤት አቅርቦ ወደራሱ ይጠራቸዋል፤ ያቀርባቸዋል። የተጠሩት ደግሞ በንዑሰ ክርስቲያንነት ደረጃ ቃለ እግዚአብሔርን እየሰሙ ከቆዩ በኋላ አዲስ ሕይወትን እንዲቀዳጁና ጸጋ መንፈስ ቅዱስን እንዲያገኙ የሚያበቃቸው ሌላ መንገድና ሥርዓት አስፈላጊ ስለሆነ ጌታ ራሱ አዘጋጅቶላቸዋል፤ ሁላችንንም በዚህ መንገድ እንድንሄድ አዞናል። መንገድ የተባለውም ቃሉን ሰምቶ መፈጸምና ያዘዘንን የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት ሁሉ መፈጸም ነው።

መዳናችን በአንድ ወቅት ተፈጽሞ የሚያልቅ ነገር አይደለም። የራሳችንና የሌሎች ክርስቲያኖችን የሕይወት ታሪክ ብንመረምር የመዳናችን ጉዳይ እስከ ሞት ድረስ በሂደት ላይ የሚገኝ መንፈሳዊ ትግል ያለበት ክርስቲያናዊ የሕይወት ጉዞ ስለሆነ በመንገዳችን ላይ መውደቅና መነሣት የማይቀር ነው። ምክንያቱም ጌታ እንዳለው "መሰናክል ግድ ሳይመጣ አይቀርም" (ሉቃ.17፥1)። ስለዚህ ለመዳናችን በርትተን መሥራት አለብን፤ ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው "በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ" (ፊልጵ.2፥12)። እንግዲህ ቃሉን ሰምተን በማመንና ቃሉን በመፈጸም እንጽና፤ "ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ" (ያዕ.1፥22)። ስለ ምሥጢራት በቃሉ የታዘዘውን እንፈጽም። ምሥጢራት ሁሉ ያለ ጸሎት እንደማይፈጸሙ እንደዚሁም ምሥጢራት በምንም ሁኔታ ያለ ቃለ እግዚአብሔር ብቻቸውን አይፈጸሙም። ስለዚህ ቃለ እግዚአብሔር፥ ጸሎትና ምሥጢራት የማይለያዩ የአንድ አካል ክፍሎች ስለሆኑ ሦስቱንም መፈጸም ክርስቲያናዊ ግዴታችን ነው።

እንግዲህ ከሦስቱ አንዱ ብቻ ማለት ቃለ እግዚአብሔርን መስማት ብቻ ይበቃኛል፤ የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ብቻ ያስፈልገኛል ሌላው ምንም አ

ያደርግልኝም ብሎ በግል ውሳኔ በቤተ ክርስቲያን ከሚፈጸመው ጸሎትና ምሥጢራት ራስን ማግለል አደገኛ ሁኔታ ነው፡፡ በመጀመሪያ የክርስቶስን ትእዛዝ ማቃለል ይሆናል፡፡ ሁለተኛ ከክርስቶስ አካል ከሆነችው ከቤተ ክርስቲያን ውጭ በመሆን ከአንዱ ቸር ጠባቂያችን ከክርስቶስና ከመንጋው ተለይቶ መቅረትን ወይም መባዘንን ያስከትልብናል፤ ከክርስቶስ መጋቢነትና ጥበቃ ውጭ በመሆን በዚህ ሆነ በኋለኛው ዓለም ለሚመጣው አደጋ ሁሉ እንጋለጣለን፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው የአንድ ሀገር ዜጋ ሆኖ ሳለ በብቸኝነት የሀገሩን ሕግ ትቶ ጎብረተሰቡን ረስቶ ራሱ በራሱ በግለኝነት ላወጣው ሕግ እንጂ ለሌላ አልገዛም ብሎ በሀገር ውስጥ መኖር እንደማይቻል እንዲሁም አንድ ክርስቲያን የሀገረ እግዚአብሔር ዜጋ ሆኖ ከቤተ ክርስቲያን ሕግ ውጭ መኖር አይቻለውም፡፡ ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን የሰማያዊውን የእግዚአብሔር መንግሥት ወክላ የምትሠራ እርሷ ናትና፤ በየጊዜው የምታውጀው ሕጓም የመንግሥተ ሰማያት ሕግ ነውና፡፡

ከቤተ ክርስቲያን የጸሎት ሕይወት መለየት ሦስተኛ ችግርን ያስከትላል፡፡ ይኸውም በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን በኩል ከሚገኘው ጸጋ በመራቅት ክርስቲያናዊ ሕይወታችን እየጐደፈ ይሄደል፤ በመጨረሻም የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ረድኤት እየተለየን ከቀቢጸ ተስፋ እንደርሳለን፡፡ ስለዚህ ከዚህ ሁሉ ለመዳን ሦስቱንም ሳንነጣጥላቸው ሁሉንም በአግባቡና በሥርዓቱ ብንፈጽማቸው እንጠቀማለን እንጂ አንጐዳም፡፡ ቃለ እግዚአብሔርን በመስማት፥ ጸሎትን በማድረግና ምሥጢራትን በመፈጸም ሕይወታችንን ከቤተ ክርስቲያን ሕይወት ጋር አንድ በማድረግ ብንኖር የክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔር ፍቅር የመንፈስ ቅዱስ ጎብረት ከእኛ ጋር ይሆናል፡፡

2. ለመዳናችን ጥምቀትን እንድንፈጽም ታዟል

ወንጌልን ለዓለም ሁሉ እንዲያስተምሩ ያዘዘ ክርስቶስ የተቀደሱ ምሥጢራትንም እንዲፈጽሙ ሐዋርያትን አዟቸዋል፡፡ "እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም፥ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ" (ማቴ.28፥19-20) በማለት ጌታችን ያዘዘው <u>ማስተማርን ብቻ ሳይሆን ማጥመቅንም ጭምር</u> እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ስለዚህ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ክርስቶስ ከእኛ ጋር ማለት ከቤተ ክርስቲያን ጋር ሁልጊዜ እንዳለ በማመን ወንጌልን በማስተማርና ምሥጢረ ጥምቀትን በመፈጸም ትእዛዙን እንጠብቃለን፡፡

"ያመነ የተጠመቀም ይድናል" (ማር.16፥16) በማለቱ ደግሞ በምሥጢረ ጥምቀት ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ተካፋይ መሆናቸውን በማመን ለተጠመቁ ሁሉ የክርስቶስ የማዳን ጸጋው እንደሚሰጣቸው ያመለክታል፡፡ ጌታም ራሱ መጠመቁ እኛ እንድንጠመቅ ለማድረግና የእርሱንም የጸጋ ምሥጢራት ለመቀበል እንድንበቃ የሚያስችል ሥርዓት መሥራቱን መዘንጋት የለብንም፡፡ ጌታ ሥራውን የጀመረው በጥምቀቱ ነው፤ ጥምቀቱም እኛን ከኃጢአትና ከሞት ያዳነበት የሞቱና የትንሣኤው ምሳሌ ነው (ሉቃ.12፥50)፡፡ ስለዚህ ይህን አምነን በምንጠመቅበት ጊዜ በሕማሙና በሞቱ የተገኘው የማዳን ሥራ ፍሬ፥ ጸጋው ይደርሰናል፤ ይህም ማለት በኃጢአት ከመጣብን ከመርገመ ሥጋና ከመርገመ ነፍስ ፈጽሞ እንድናለን፡፡

ሰው ሁሉ ሕፃናትም ጭምር በጥንተ አብሶ ከመጣው መርገምና ፍዳ ነፃ አይደሉም፡፡ በጥንተ ተፈጥሮ የነበረው ጸጋ ስለ ተገፈፈ በሐዲስ ተፈጥ

www.eotc-mkidusan.org

ሮ የመዳን ጸጋ ያስፈልጋቸዋል፡፡ የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን በተሳሳቱ ጊዜ የ ነበራቸውን ጸጋ አጡ፥ ከቀደመው ክብራቸው ወረዱ፥ በልዩ ልዩ መከራ ውስጥ ወደቁ፡፡ "በክርስቶስ ሞት በተደረገው እርቅ ደግሞ አዳምና ሔዋን ወደ ጥንት ቦታቸው እንዲመለሱ ተፈቅዶላቸው የአዳምና የሔዋን ልጆችም እንደየ ጸታቸው በአርባ በሰማንያ ቀናቸው ሲጠመቁ በዘር ከወረደው መርገም ይገላገላሉ፡፡ የቀደሙ ወላጆቻችን ያስወሰዱት የጸጋ ልጅነት በጥምቀት ይመለስላቸዋል፡፡ ከቀ ኑ አቆጣጠር በቀር ይህ በሁሉ የታወቀ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ነው" በማለት ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ስለ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የጻፉትን ተመልከት (<u>ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት፣</u> በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕ ዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች መምሪያ፣ በማኅበረ ቅዱሳን ትምህርት ክፍል፣ በየሰንበት ት/ቤቶች ለሚማሩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማስተማሪያ የተዘጋጀ፣ 1993 ዓ.ም.፣ ገጽ 43)፡፡

በኃጢአታችን ምክንያት ከመጣብን የፍርድ ቅጣት በውኃ በመጠመቅ መዳናችንን ለማስረዳት ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ከብሉይ ኪዳን ታሪክ በመጥቀስ ታሪክና ምሳሌውን ከአማናዊው ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው ተርጉሞ ያስረዳናል፡፡

> "ጥቂቶች ማለት ስምንት ነፍስ በውኃ የዳኑበት መርከብ ሲዘጋጅ፥ የእግዚአ ብሔር ትዕግሥት በኖኅ ዘመን በቆየ ጊዜ ቀድሞ አልታዘዙም፡፡ <u>ይህም ውኃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል"</u> ካለ በኋላ በውኃ ተጠምቆ መዳን ምን ማለት እንደሆነ ሲገለጽ "የሰውነትን እድፍ ማስወገድ አ ይደለም፥ ለእግዚአብሔር የበጎ ኅሊና ልመና ነው እንጂ፥ ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ነው" ብሏል (1ኛ ጴጥ.3፥20-21)፡፡

የክርስትና ጥምቀት እንደ መጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት አይደለም፡፡ የክርስትና ጥምቀት በውኃ ብቻ አይደለም፡፡ በውኃ መጠመቅ ማለት በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ማለትም ነው፡፡ በውኃና በመንፈስ በምንጠመቅበት ጊዜ ከኃጢአታችን ድነን አዲስ ልደትን እናገኛለን፤ የክርስቶስ ትንሣኤ ተካፋይ እን ሆናለን (ዮሐ.3፥5፤ ሮሜ.6፥3-5)፡፡ የተጠቀሰው ሐዋርያ እንዳለው ጥምቀት የ ሰውነትን እድፍ ለመታጠቢያ አይደለም፡፡ በውኃና በመንፈስ ማለት በክርስቶስ መንፈስ በመጠመቃችን ከሙታን ከተነሣው ክርስቶስ ጋር አንድ መሆናችን ትንሣኤ ልቡና፥ በጎ ኅሊና፥ አዲስ ሕይወትን ከእርሱ እንደምናገኝ ያስረዳናል፡፡ በጥምቀት መዳን ማለት በዚህና በመሳሰሉት ይተረጐማል፡፡

እንግዲህ ጥምቀት የክርስትና እምነት ምሥጢር ነው፤ የመዳናችንም ጸጋ ነው፡፡ የመዳናችን ምሥጢር በክርስቶስ ነው፤ ጥምቀት ደግሞ ከአዳኛችን ጋር አንድ ያደርገናል (ሮሜ.6፥3-5)፡፡ ከአዳኛችን ከመድኃኒታችን ጋር አንድ ከሆንን ከእርሱ የመዳንን ጸጋ ከኃጢአት ቁስል የመፈወስ ሀብትን እናገኛለን፡፡ ስለዚህ ጥምቀት እኛን ከክርስቶስ ጋር አንድ በማድረግ የደኅንነትን ጸጋ የሚያ ሰጠን በግብረ መንፈስ ቅዱስ የሚከናወን ታላቅ ምሥጢር ነው፡፡

<u>3. የዕለተ ዓርቡ የማዳን ሥራ በሥጋውና በደሙ</u>

በዕለተ ዓርብ ባደረገው ተልእኮ ጌታችን ለዓለም ሁሉ ለአንዴና ለዘላለም የፈጸመውን የማዳን ሥራውንና አምላካዊ ጸጋውን እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ በየዘመኑ የሚነሡት ትውልድ ሁሉ በቀላሉ አግኝተው የሚድኑበትን መንገድ አ ዘጋጅቷል፡፡ ይህንንም የማዳን ሥራ የሚያከናውኑለትን ሐዋርያቱንና ተተኪዎቻቸውን፥ ቤተ ክርስቲያኑንና ምሥጢራቱን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መሥርቷል፥ አደራጅቷል፡፡ ዛሬም የማዳን ሥራውን የሚሠራ እርሱ ራሱ

www.eotc-mkidusan.org

ባለቤቱ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከቤተ ክርስቲያኑ ጋር በመሆን ነው (ማቴ.28፡19-20)።

በአርአያውና በአምሳሉ በክብር የፈጠረው ሰው የፈጣሪውን ቃል ኪዳን አፍርሶ በኃጢአትና በጨለማ ወድቆ በነበረ ጊዜ ጌታ የወደቀውን ሰው ወደ ቀደመ ክብሩ ለመመለስ ሰው በመሆን በሥጋ መጥቶ በሥጋው የበደለኛውን የሰውን ሕማምና ሞት ተቀብሎ በሞቱ ሞትን ደምስሶ በትንሣኤው አዲስ ሕይወትን በመስጠት አዳነው። ስለዚህ ጉዳይ ነገረ መስቀሉንና ትንሣኤውን በገለጽንበት አንቀጸ ሃይማኖት በክፍል አንድ ተመልክተናል። ከዚህ ደግሞ የዕለተ ዓርቡ የማዳን ሥራው እስከ ዕለተ ምጽአት ለሚነሡት ሁሉ የመዳናቸው ምሥጢር እንዴት በሚታይና በሚጨበጥ መንገድና ሁኔታ በቃሉ አገልግሎትና በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን እንደሚፈጸም ለማስረዳት እንሞክራለን። ቀድሞውንም በማይታየው ባሕርዩ ቃለ እግዚአብሔር ወልድ እኛን ለማዳን ወደዚህ ዓለም ሲመጣ በሚታይና በሚጨበጥ መንገድ በሥጋው ተገልጸ ነው። አሁንም እንደ ቀድሞው ለእኛ እንደሚስማማ በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አማካይነት በተለይም በምሥጢረ ቁርባን በሚታይና በሚጨበጥ መንገድ የሕይወት ምግብ ሆኖ እኛን ለማዳን ቀርቧል። የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንም ትርጉም ይኸው ነው፤ በሚታየው ነገር የማይታየውን ጸጋ የምናገኝበት መንገድ ነው።

ለአንዴና ለዘላለም የተፈጸመው ታላቁ የዕለተ ዓርብ የማዳን ሥራው ለዓለም ሁሉ እንዲዳረስ የምሥራቹን ቃል ወንጌልን እንዲያስተምሩ፥ በስሙ ንስሐና የኃጢአት ሥርየትን እንዲሰብኩ፥ ምሥጢራትንም እንዲፈጽሙ ጌታ ሐዋርያትን አዟቸዋል (ማቴ.28፡19-20፤ 1ኛ ቆሮ.11፡23-26፤ ሉቃ.24፡47፤ 22፡19-20)። ስለዚህ ነው ሐዋርያት ቃሉን ካስተማሩና ካሳመኑ በኋላ በማጥመቅ፥ እጃቸውን በመጫን፥ በማቁረብ የጸሎትና የቃሉን አገልግሎታቸውን በትጋት ይፈጽሙ እንደ ነበር የተጻፈው (የሐዋ.2፡37-42፤ 6፡4፤ 8፡14-17)። ይኸን ሁሉ ከጌታ ተምረውታል፤ በተለይም ስለ ምሥጢረ ቁርባን ሰፋ ያለ ትምህርት ተሰጥቷቸዋል።

ከሰማይ ስለ ወረደው የሕይወት እንጀራ ምሥጢር (ዮሐ.6)

ሥርዓተ ቁርባንን ካቋቋመበት ከስቅለት ዓርብ ዋዜማ ከምሴተ ኀሙስ በፊት ሁለት ዓመት ያህል ቀደም ብሎ ከሰማይ ስለ ወረደው የሕይወት እንጀራ ምሥጢር፥ ስለ ሥጋውና ደሙ ምሥጢር ጌታ በሰፊው ለሕዝቡ አስተምሯል። ይህም በወንጌል ዮሐንስ ምዕራፍ ስድስት ተመዝግቦ ይገኛል። በምዕራፉ መጀመሪያ ላይ እንደ ተጻፈው ጌታ አምስቱን የገብስ እንጀራና ሁለት ዓሣ በተአምራት አበርክቶ አምስት ሺህ ሕዝብ ያህል እንደ መገበ ይገልጻል። ይህም ተአምራዊ ድርጊት ለምሥጢረ ቁርባን ትምህርት በር ከፋች ማለት መግቢያ ሆኗል። በዚህ መነሻነት የተበረከተውን እንጀራ የበሉት ሰዎች በማግሥቱ ጌታን ፈልገው አገኙት። ሕዝቡም ጌታን የፈለጉበት ምክንያት ስለበሉና ስለጠገቡ እንጂ ተአምራቱን፥ ምልክቱን በማየት እንዳልነበረ ማእምረ ኅቡዐት ጌታ ገልጾ ነግሯቸዋል (ዮሐ.6፡26)። ቁም ነገሩ ይህን ተአምር የፈጸመው እርሱ ማን እንደሆነ መመርመርና በእርሱም ማመን ነበር። የእነርሱ ፍላጐት ግን ማንም ይሁን ማን የሚያበላቸውና የሚያጠግባቸው መሪ ንጉሥ መፈለግ እንጂ የተአምራቱን፥ የምልክቱን ትርጉም ከማወቁና ከማመኑ አልነበረም (ዮሐ.6፡15)። ስለዚህ ጌታ "ለሚጠፋ መብል አትሥሩ፤ ነገር ግን ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር መብል የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ሥሩ . . . የእግዚአብሔር ሥራ እርሱ በላከው እንድታምኑ ነው አላቸው" (ዮሐ.6፡27-29)።

እነርሱ ግን ያዩትን ምልክት ትተው ሌላ ምልክት ፈለጉ፤ ሥራህን አይተን እናምንብህ ዘንድ ምን ምልክት ታሳየናለህ? ምንስ ሥራ ትሠራልናለህ? ከሰማይ እንጀራ ሰጣቸው ተብሎ እንደ ተጻፈ አባቶቻችን በበረሃ ሳሉ መና በሉ አሉት። ጌታም፦ "እውነተኛ እንጀራ ከሰማይ የሚሰጣችሁ አባቴ ነው እንጂ ከሰማይ እንጀራ የሰጣችሁ ሙሴ አይደለም፤ የእግዚአብሔር እንጀራ ከሰማይ የሚወርድ ለዓለምም ሕይወት የሚሰጥ ነውና አላቸው" (ዮሐ.6፥32-33)። ተከራካሪዎቹ አይሁድ ግን የሚፈልጉት ለሆድ የሚሆን እንጀራ በየቀኑ እንደ ቀድሞ አባቶቻቸው ስለሆነ እንዳይራቡ ይህን ዓይነት እንጀራ ዘወትር እንዲ ሰጣቸው ጠየቁት። ጌታ ግን ከሰማይ የወረደ የሕይወት እንጀራ እርሱ ራሱ እን ደሆነና እርሱንም ካመኑት እንደማይራቡና እንደማይጠሙ ነገራቸው። እነርሱ ግን አላመኑትም፤ የነገራቸውንም ቃል አልተቀበሉትም፤ እንዲያውም ተቃውሟቸውን በማከረር ይህ የምናውቀው የዮሴፍ ልጅ አይደለም እንዴ! "ከ ሰማይ የወረደ እንጀራ እኔ ነኝ" እንዴት ይለናል በማለት አንጉራጉሩበት (ዮሐ.6፥41-42)። ምግበ ነፍስን ትተው ምግበ ሥጋን ብቻ እንደሚፈልጉ ገና ከመጀመሪያው ጌታ ያውቅ ነበርና (ዮሐ.6፥26) ለነፍሳቸውና ለዘላለማዊ ሕይወታቸው የሚያስፈልገውን ምግብ የሚያገኙበትን መንገድ በግልጽ ነግሯቸዋል፤ ይኸውም በመጀመሪያ የእርሱን ማንነት አውቆ ማመንና ለቃሉም መታዘዝ፥ ከዚያም የዘላለም ሕይወት የሚሰጠውን እንጀራ ማወቅና መቀበል ነበረ። እነርሱ ግን የነገራቸውን ሁሉ እንደገና በይበልጥ ተቃወሙት እንጂ አል ተቀበሉትም።

ጌታም በተከራካሪዎቹና በተቃዋሚዎቹ መካከል ትምህርቱን በማጠናከር እርሱ ከሰማይ የወረደ የሕይወት እንጀራ መሆኑን እንዲያምኑ በቀጥታ ነገሩን እያረጋገጠ ይገልጽላቸው ጀመር። "የሕይወት እንጀራ" የተባለ ውም ምን እንደሆነ በስውር ሳይሆን በግልጽ እየደጋገመ በአጽንኦት ለተከራካ ሪዎቹም ለደቀ መዛሙርቱም ለሐዋርያቱም (ዛሬ ላለነው ለእኛም) በጠቅላላ በዓ ለም ውስጥ ላለነው ሁሉ እንደሚከተለው ያስረዳናል።

> " . . . እኔም ክርስቶስ ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው።" በማለት የተቀደሰውን ምሥጢር ለገዛ ወገኖቹ ገለጸላቸው። እነርሱ ግን እንደ ዛሬዎቹ ተቃዋሚዎች የምሥጢሩ ኃይለ ቃል ቢገባቸውም ባይገባቸውም ከመከራከርና ከመቃወም በቀር ፍሬ ነገሩን ለመቀበል አይፈልጉም። ስለዚህ "አይሁድ፦ ይህ ሰው ሥጋውን ልንበላ ይሰጠን ዘንድ እንዴት ይችላል? ብለው እርስ በእርሳቸው ተከራከሩ። ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው እውነት እውነት እላችኋለሁ የወልደ እጓለ እመሕያው ክርስቶስን ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካል ጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ። ሥጋዬ እው ነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ። ሕያው አብ እንደላከኝ እኔም ከአብ የተነሣ ሕያው እንደምሆን እንዲሁ የሚበላኝ ደግሞ ከእኔ የተነሣ ሕያው ይሆናል። ከሰማይ የወረደ እንጀራ ይህ ነው፤ አባቶቻችሁ መና በልተው እን ደሞቱ አይደለም፤ ይህን እንጀራ የሚበላ ለዘላለም ይኖራል (ዮሐ.6፥51-58)።

እንግዲህ ከዚህ የሕይወት ቃል እንደምንማረው ለዓለም መድኃኒት ሆኖ የሚሰጠው የጌታ ሥጋና ደም እንደሆነ በማያሻማ ቋንቋ በግልጽ ተነግሯል፤ ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር አይደለም። ምሳሌያዊ አነጋገር ቢሆንማ አይሁድ ይህ ሰው ሥጋውን ልንበላ ይሰጠን ዘንድ እንዴት ይችላል? ብለው ባላጉረመረሙም ነበር። ከዚያም በኋላ ከተቃዋሚዎቹ ከአይሁድ ወገን ሳይሆን "ከደቀ መዛሙርቱም ብዙዎች በሰሙ ጊዜ፥ ይህ የሚያስጨንቅ ንግግር ነው ማን ሊሰማው ይችላል?" ብለዋል (ዮሐ.6፥60)። ጌታ ሥጋውን እውነተኛ ምግብ

ደሙን እውነተኛ መጠጥ አድርጎ ሊሰጠን እንደሚችል ማመን ይቀድም ነበር፤ እነርሱ ግን አላመኑትም። ቀደም ብሎ ለምግበ ሥጋ የሚሆነውን ጌታ በተአምር ጎብስቱን አበርክቶ መመገቡ ለምግበ ነፍስ የሚሆነውን የሕይወት እንጀራ ሥጋውና ደሙን እንደዚሁ በተአምር ይሰጠናል ብለው እንዲያምኑ ነበር። እርሱ ውኃውን ወደ ወይን የለወጠ ሌሎችንም ብዙ ተአምራት ያደረገ ይህንንም በተአምር ማድረግ ይችላል ብለው ቃሉን ተቀብለው ስለ ሕይወት እንጀራ ምሥጢር እንዲያስረዳቸው ደቀ መዛሙርት እንደ መሆናቸው መጠን ሊጠይቁት በተገባ ነበር እንጂ የዮሴፍ ልጅ ነው ከሚሉት ተቃዋሚዎች ጋር ሆነው ማንጐራጐር አያስፈልጋቸውም ነበር። ተቃዋሚዎቹ ከሰማይ የወረደ ከድንግል የተወለደ መሆኑን የካዱና ምሥጢረ ሥጋዌን የማያምኑ ነበሩ። ላመኑት ግን ክርስቶስ ማለት ሥጋ የሆነ ቃል ነው። ከሰማይ የወረደው የሕይወት እንጀራ የእግዚአብሔር ቃል የተዋሐደው ሥጋ እንደሆነ ከእግዚአብሔር የተማሩት ሁሉ ያውቃሉ።

<u>የዕሩቅ ብእሲ ሥጋ ሕይወት አይሰጥም፥ አይጠቅምም</u>

መለኮታዊ ቃል ያልተዋሐደው ሥጋ ብቻውን የሕይወት እንጀራ አይባልም፤ ሥጋ ብቻውን ሕይወት አይሰጥምና። ስለዚህ ነው ጌታ "ሕይወት የሚሰጥ መንፈስ ነው ሥጋ ምንም አይጠቅምም፤ እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው ሕይወትም ነው" ያለው (ዮሐ.6፥63)። ይህን ኃይለ ቃል ጌታ የተናገረው የእርሱን አምላክነት ለማያምኑ ሁሉ ነው፤ በተለይም ዕሩቅ ብእሲ ወልደ ዮሴፍ ለሚሉት ተቃዋሚዎች ነው። በእርግጥም የዕሩቅ ብእሲ ሥጋ ለመንፈሳዊ ነገር አይጠቅምም። ስለሆነም ከላይ ከጥቅሱ እንደምናየው ጌታ "ሥጋዬ" አላለም እንዲያው በአጠቃላይ አነጋገር "ሥጋ ምንም አይጠቅምም" ነው ያለው። ይህም ማለት መንፈሳዊነት የሌለው የምድራዊነት የሥጋዊነት ባሕርይ ብቻ መሆኑን የሚያስገነዝበን ነው፤ "ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው" ተብሎ እንደ ተጻፈው (ዮሐ.3፥6)። በአጠቃላይ የተፈጥሮ ሰው ሥጋ ማለት እንጂ መለኮት የተዋሐደውን የጌታን ሥጋ ማለት እንዳልሆነ ማስተዋል ያስፈልጋል። በጥንተ ተፈጥሮ የነበረው የፊተኛው አዳም ሥጋ ሳይሆን የኋለኛው አዳም ነው ሕይወትንና መንፈስን የሚሰጠን። "ፊተኛው ሰው አዳም ሕያው ነፍስ ሆነ ተብሎ ተጽፏል፤ ኋለኛው አዳም ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ" የተባለውን ማነፃፀር ይጠቅማል (1ኛቆሮ.15፥45)። ጌታ ስለ ራሱ ሥጋ ሲናገር "ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ <u>ሥጋዬ</u> ነው" ብሏል (ዮሐ.6፥51)። የእርሱ ሥጋ ሕይወትን ሊሰጥ የሚችል መንፈስም ሕይወትም ያለበትን ቃል የተዋሐደ ሥጋ ነው። የጌታ ሥጋ መለኮታዊ ቃል የተዋሐደው ስለሆነ በመስቀል ላይ መሥዋዕት በመሆን አድኖናል፤ የዘላለም ሕይወትንም ሰጥቶናል።

ከሰማይ የወረደ እውነተኛ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ በማለቱ ደቀ መዛሙርቱ ሳይቀሩ የተሰናከሉበት ምክንያት የእርሱን ማንነትና አመጣጡም ከየት እንደሆነ በትክክል ባለማወቃቸው ነው። ስለዚህ ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ "ይህ ያሰናክላችኋልን? እንግዲህ የሰው ልጅ አስቀድሞ ወደነበረበት ሲወጣ ብታዩ እንዴት ይሆናል?" ብሎ በአንክሮና በጥያቄ ምላሽ የሰጣቸው። እዚህ ላይ ጌታ ስለ ዕርገቱ የጠቀሰው ከሰማይ የወረደው እርሱ ራሱ መሆኑን ለማመልከት ነው። በዕርገቱ ርደቱ (መውረዱ) ይታወቃልና። አንድም "ከሰማይ ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም" ብሎ ለማስተማር ነው (ዮሐ.3፥13)። በኋላ ጊዜ ዕርገቱን ያዩ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ከሰማይ የወረደው እርሱ ክርስቶስ ብቻ እንደሆነ አምነዋል። ከሰማይ የወረደ እውነተኛ የሕይወት እንጀራም እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ አውቀዋል። ሥጋውም እውነተኛ እንጀራ ደሙም እውነተኛ መጠጥ እንደሆነ አምነው ተቀብለውታል። እስከዚያው ቀን ድረስ ግን ነገሩ

www.eotc-mkidusan.org

ስላልገባቸውና ስላስጨነቃቸው ተሰናክለውበታል።

ጌታ በሥጋው ወደ ሰማይ ያረገው የዕለተ ዓርቡን ተልእኮ ከፈጸመ በኋላ ነው። ከሰማይ የወረደውና ሥጋ የለበሰው ኃጢአትንና ሞትን አስወግዶ የዘላለም ሕይወትን ሊሰጠን ስለሆነ በመስቀል ላይ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ የመስቀልን መሥዋዕትነት ተቀብሏል። ሥርየተ ኃጢአት አግኝተን መዳናችንና የዘላለም ሕይወት መውረሳችን በመስቀል ላይ ለቤዛ ዓለም በተሠዋው ሥጋና ደም ስለሆነ ሥጋው እውነተኛ የሕይወት እንጀራ ደሙም እውነተኛ የሕይወት መጠጥ መሆኑን አምነን እንድንቀበለው ጌታችን ያስተማረው ገና ከጥምቀቱ በኋላ በነበረው በሁለተኛው የአይሁድ ፋሲካ ነበር (ዮሐ.6፥4)። ስለ ሕማሙና ሞቱ፥ ስለ ትንሣኤውና ዕርገቱ ደቀ መዛሙርቱ ገና የማያውቁ ስለሆነ ስለ ሕይወት እንጀራ ጌታ ያስተማረው ሁሉ እጅግ አስ ጨንቋቸው ነበር። "ከዚህም የተነሣ ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎቹ ወደ ኋላ ተመለሱ ወደፊትም ከእርሱ ጋር አልሄዱም" (ዮሐ.6፥66)። አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ግን በእምነት ጸንተው የሕይወት ቃል ከእርሱ ጋር ብቻ መሆኑን መስክረው ከእርሱ አልተለዩም ነበር (ዮሐ.6፥67-69)።

<u>የሕይወት እንጀራ ምሥጢር በጸሎተ ኀሙስ</u>

ስለ ሥጋውና ደሙ ጌታ የተናገረውን ቃል ሁሉ ሐዋርያት ቢያም ኑም ሥጋው እውነተኛ መብል ደሙም እውነተኛ መጠጥ ሆኖ እንዴትና መቼ እንደሚያገኙት ገና አያውቁም ነበር። ጌታ ግን መዋዕለ ትምህርቱን ማለት የሦስት ዓመት ከሦስት ወር ሥራውን ጨርሶ የዕለተ ዓርቡን ተልእኮ የሚፈጽምበት ሰዓትና ጊዜው ሲደርስ ምሥጢሩን ገለጸላቸው። በቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት አቆጣጠር አራተኛው የአይሁድ ፋሲካ ሲደርስ ጌታ "ከዚህ ዓለም ወደ አብ የሚሄድበት ሰዓት እንደ ደረሰ አውቆ በዚህ ዓለም ያሉትን ወገኖቹን የወደዳቸውን እስከ መጨረሻ ወደዳቸው" (ዮሐ.13፥1)። ለውጮቹ ሳይሆን ለእነዚህ ማለት ለሐዋርያቱ በመጀመሪያ የመንግሥተ ሰማያትን ምሥጢር በኋላም የሥጋውንና የደሙን ምሥጢር ገልጸላቸዋል (ማቴ.13፥11፤ ማር.14፥22-24)። ስለ ኃጢአታችን ሥርየት በስቅለት ዓርብ ለዓለም ሁሉ መድኃኒት እንዲሆን በመስቀል ላይ ለእንዴና ለዘላለም መሥዋዕ ት አድርጎ ያቀረበውን ሥጋውና ደሙን ሁልጊዜ እንዲያገኙትና በእውነተኛ የሕይወት ምግብነት እንዲቀበሉት ሕግና ሥርዓትን ሠርቶላቸዋል። ይህንንም እንደ አይሁድ ቀን አቆጣጠር በዕለተ ዓርብ የመጀመሪያው ክፍለ ጊዜ ማለት በእኛ አቆጣጠር በስቅለት ዋዜማ በጸሎተ ኀሙስ ማታ ሥጋውን እውነተኛ ምግብ ደሙንም እውነተኛ መጠጥ አድርጎ ሰጥቷቸዋል። በዚያች ምሽት የኦሪትን የእንስሳት መሥዋዕት፥ የአይሁድን የፋሲካ እራት ለመጨረሻ ጊዜ ፈጽሞ አማናዊውን፥ መዳንንና የዘላለም ሕይወትን ያገኘንበትን መሥዋዕት የራ ሱን ሥጋና ደም አቅርቦላቸዋል። ይህንንም ታላቅ ሥራ ያከናወነው ኀብስ ቱን አንሥቶ ባርኮ ቆርሶ ይህ ሥጋዬ ነው ብሎ፤ ጽዋውንም እንደዚሁ አንሥቶ ባርኮ ይህ በመስቀል ላይ ለኃጢአት ሥርየት የሚፈሰው ደሜ ነው ሁላችሁም ከዚህ ጠጡ ባላቸው ጊዜ ነበር (ማቴ.26፥26-30)። ጌታ በሥጋው መሥዋዕት ነት በሞቱ ያዳነን መሆኑን እያሰብን ይህን የሠራልንን ሕግና ሥርዓት እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ እንድናደርገው አዞናል (ሉቃ.22፥19-20፤ 1ኛቆሮ. 11፥23-25)። ስለዚህ ዛሬ ከቤተ ክርስቲያን በአርአያ ኀብስት የምንቀበለው የክርስቶስ ሥጋ፥ በአርአያ ወይን የምንቀበለው የክርስቶስ ደም መሆኑን አምነን የመዳናችን ምሥጢር የሚፈጸምበትን አምላካዊ ጸጋ እናገኛለን።

እንግዲህ መዳናችን በጌታ ሥጋ ነው። ምክንያቱም ይህ አካላዊ

www.eotc-mkidusan.org

ቃልን የተዋሐደ ሥጋ ነው የኃጢአታችንን የሞት ቅጣት የወሰደው፡፡ ይህ የጌታ ሥጋ ነው ሞትን ሽሮ ከመቃብር የተነሣው፡፡ ታዲያ ከዚህ ከመለኮታዊ ሥጋ ጋር አንድነት ከሌለን አንድንም፡፡ ስለዚህ በጥምቀት ከጌታ ጋር አንድ ሆነናል፤ በመንፈስ ቅዱስ ኃይልም የሞቱና የትንሣኤው ተካፋይ ለመሆን ችሎታውን ሰጥቶናል፡፡ እንደዚሁም በቅዱስ ቁርባን ከእርሱ ጋር አንድነታችንን በማጽናት ሕይወትንና ትንሣኤ ዘለክብርን በማግኘት ከእርሱ ጋር እንኖራለን፡፡ ምክን ያቱም "ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፤ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ . . . በእኔ ይኖራል፤ እኔም በእርሱ እኖራለሁ" ብሏልና (ዮሐ.6፥53-56)፡፡ አለበለዚያ ሥጋውና ደሙን ካልተቀበልን ሞት እንጂ ሕይወት የለንም፡፡ ምክንያቱም "የወልደ እጓለ እመሕያው ክርስቶስን ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም" ተብሎ ተጽፏልና (ዮሐ.6፥53)፡፡ እንግዲህ ብዙዎቹን የጌታን ደቀ መዛሙርት ያስጨን ቅ የነበረው ከሰማይ የወረደው የሕይወት እንጀራ ምሥጢር በጸሎተ ኀሙስ ማታ በተፈጸመው በቅዱስ ቁርባን ሥርዓት በእምነት ለጸኑት ለአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ብቻ እንዲታወቅ ሆነ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የዕለተ ዓርቡ የማዳን ሥራ በሥጋውና በደሙ ምሥጢር በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አማካይነት እን ዲቀጥል ተደረገ (የሐዋ.ሥራ 2፥42)፡፡

ቅዱስ ቁርባን - የምሥጢራት ሁሉ መክብባቸው

የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ የበላያቸው፥ መክብባቸውና መፈጸሚያቸው የሆነው ቅዱስ ቁርባን በጌታ ትእዛዝ ጸሎተ ኀሙስ ማታ መመሥረቱ ከላይ ተገልጧል (ሉቃ.22፥14-20)፡፡ ምሥጢረ ቁርባን ከሁሉ በላይ የሆነበት ምክንያት ጌታ የሰውን ልጆች ለማዳን በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ ሥጋውን በመቁረስ ደሙን በማፍሰስ ካሣ የከፈለበትን፥ የማዳን ሥራውን የፈጸመበትን ሁኔታ የሚያረጋግጥና የሚመሰክር ከመሆኑ ጋር አማኞች ከሥጋውና ከደሙ ተካፋይ እንዲሆኑ በማብቃት የሕይወትን ጸጋ እንዲቀበሉ ስለሚያደርግ ነው፡፡ ስለዚህም የሌሎቹ ምሥጢራት ሁሉ በቅዱስ ቁርባን አማ ካኝነት የምሥጢራቸውን ትርጉምና ፍጻሜ ያገኛሉ፡፡

ምሥጢረ ቁርባን የሚከናወንበት ጸሎተ ቅዳሴ እጅግ የከበረና ለክርስቲያኖች ሁሉ ጸጋና በረከትን የሚያሰጥ ነው፡፡ የዝግጅቱ ክፍል ሳይቆጠር ጸሎተ ቅዳሴ ሁለት ዐበይት ክፍሎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ቃለ እግዚአ ብሔር የሚሰማበትና ትምህርተ ወንጌል የሚሰጥበት ጊዜ ነው፡፡ ሁለተኛው መሥዋዕተ ቁርባን የሚፈጸምበት ነው፡፡ ስለዚህ ጸሎተ ቅዳሴ ሥርዓተ አም ልኮት ብቻ ሳይሆን ስብከተ ወንጌል የሚካሄድበት፥ ክርስቲያናዊ ፍቅርና ሰላም የሚመነጭበት፥ መልካም ሥራ የሚወጠንበትና የሚፈጸምበት በመሆኑ ቤተ ክርስቲያን ከምታከናውናቸው መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶች ሁሉ ከፍተ ኛውን ቦታ ይዞ ይገኛል፡፡ በኦሪቱ ሥርዓት በቤተ መቅደስ ይፈጸም የነበረው የብሉይ ኪዳን መሥዋዕት በቅዱስ ቁርባን በመተካቱ ለሐዲስ ኪዳኑ የአምልኮት ሥርዓትና ምሥጢር ሁሉ መሠረት ከመሆኑም ጋር ጌታ ዳግመኛ እስኪመጣ ድረስ የክርስቶስ የሞቱና የትንሣኤው ምስክር ሆኖ ይቆያል፡፡ መሥዋዕት ከሆ ነልን ከሐዲስ ኪዳኑ የፋሲካ በግ ከክርስቶስ ጐን በዕለተ ዓርብ የፈሰሰው ደምና ውኃ የመዳንና የጽድቅ ጸጋ ምሥጢራት ሁሉ ምንጭ በመሆኑ ይህን የመሥዋዕ ት ምሥጢር በምትፈጽም ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ጸጋ በብዛት ይሞላባታል፡፡

የወንጌልን ቃል አምነው ምሥጢረ ቁርባንን የሚቀበሉ አማኞች ሁሉ የክርስቶስ የጸጋው ምሥጢር ተካፋይ ይሆናሉ፡፡ እነርሱ ጌታ ኀብስቱን አንሥቶ ባርኮና ቆርሶ ለደቀ መዛሙርቱ ሲሰጣቸው "እንካችሁ፥ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው"

www.eotc-mkidusan.org

ብሎ የተናገረውን፡ እንዲሁም ጽዋውን አንሥቶና አመስግኖ ሲሰጣቸው "ሁላችሁም ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የሐዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው" ያለውን ቃለ ወንጌል (ማቴ.26፡26-28) አምነው ክርስቶስ በመካከላቸው ተገኝቶ ዛሬውኑ እንደ ፈጸመው አድርገው በመቀበላቸው በእውነት የመዳኑ ጸጋ ለእነርሱ ደርሷቸዋል፡፡ ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው የተባለውም በእነርሱ ላይ ይፈጸማል (ዮሐ.6፡53)፡፡ ነገር ግን ሳያምኑ የሚቀበሉትና በመጠራጠር የሚተውት ሁለቱም ከመዳን ጸጋ ውጭ ናቸው፡፡ ምክንያቱም እነርሱ ገና በምሥጢረ ሥጋዌ አላመኑም ማለት ነው፡፡

ጸጋ እግዚአብሔር ለሰዎች ልጆች የተሰጠው ቃለ እግዚአብሔር ወልድ በሚታይና በሚዳሰስ በሥጋ ሰውነት በመምጣቱ ነው፡፡ በሰውነቱ ሕማማትን በመቀበል፡ እኛን በማጽደቅ፡ በቅዱስ ደሙ ፈሳሽነት ከኃጢአታችን በማንጻትና ከእግዚአብሔርም ጋር በማስታረቅ ጸጋ በጸጋ ላይ እንድንቀበል አ ብቅቶናል፡፡ እንግዲህ በሚታይና በሚዳሰስ ሰውነቱ የማይታየውን መለኮታዊ ጸጋውን እንዳንጎናጸፈን እናስተውል፡፡ እንዲዚሁም ዛሬ አካሉ በሆነችው ቤተ ክርስቲያን አማካይነት በሚታዩና በሚዳሰሱ ምሥጢራቱ የማይታየውን ረቂቁን ጸጋ መንፈስ ቅዱስን እንቀበላለን፡፡

እንግዲህ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ሥጋ ከመልበሱ የተነሣ ጸጋ እግዚአ ብሔር በሥጋውና በደሙ እንደመጣልን እንረዳለን፡፡ "ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው . . . ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እው ነተኛ መጠጥ ነውና" (ዮሐ.6፡54-55) የተባለውን የጌታን ቃል እንዴት በተግባር እንደምናውለው እስኪ በጽሞና እናስብ! ታዲያ ይህን የወንጌል ቃል ለመፈጸም ዛሬ አንድ ሰው የጌታን ሥጋና ደም ከየትና እንዴት ያገኛል? መልስ፡ በጸሎተ ኅሙስ ማታ ጌታ ምሥጢረ ቁርባንን በመሠረተ ጊዜ የትና እንዴት እንደሚገኝ ለሐዋርያት አስተምሯቸዋል (ሉቃ.22፡14-20)፡፡ ይኸውም ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን የሚገኘው ለሐዋርያት የተሰጠው የቅዱስ ቁርባን ምሥጢር ስለሆነ ምእመናን ንስሐ እየገቡ የጌታን ሥጋ እየበሉ ደሙንም እየጠጡ እንደ ወንጌሉ ቃል የዘላለም ሕይወትን ጸጋ ያገኛሉ፡፡

ይህ ምሥጢር የጸጋ ሁሉ ምንጭ ስለሆነ ሌሎቹ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ በሥጋው በደሙ ምሥጢር አማካኝነት ይፈጸማሉ፡፡ ስለዚህም እያንዳንዱ ምሥጢረ ቤተ ክርስቲያን ከጌታ ሥጋና ደም ጋር በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተያያዘና ከጌታ ሕማማ፡ሞትና ትንሣኤ ጋር የተዛመደ ስለሆነ የራሱ የሆነ ልዩ ልዩ ጸጋን የመስጠት ችሎታ አለው፡፡ ስለ ተቀደሱት ምሥጢራት እንደ ዓይነታቸውና እንደ ሁኔታቸው በየስማቸው የተገለጹ ስለሆነ በቦታቸው ላይ እንመለከታቸዋለን፡፡

ተስፋችን በጸጋ መንፈስ ቅዱስ ይጠናከራል

በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሚገኘው ጸጋ ለተስፋችን ሕይወት ይሰጠዋል፡ ያሳድገዋል፡፡ በኃጢአት የተነሣ በልዩ ልዩ ፈተናም ብንወድቅ እንኳ በምሥጢረ ንስሐ አማካይነት ተስፋችን ይታደሳል፡፡ ጌታ "ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው" ካለ በኋላ ይቀጥልና "እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ" (ዮሐ.6፡54) በማለቱ ተስፋ ትንሣኤ በምሥጢረ ቁርባን እንደሚሰጥ ያመለክታል፡፡ በጸሎተ ሃይማኖት "የሙታንን መነሣት ተስፋ እናደርጋለን የሚመጣውንም ሕይወት ለዘላለሙ አሜን" በማለት የገለጽነው እምነትና ተስፋችን ከላይ በጠቀስነው የወንጌል ቃልና ለቅዱስ ቁርባን

በተሰጠው ቃል ኪዳን አማካኝነት ይጸናል፥ ይታተማል። ተስፋ መንግሥተ ሰማያትን ጸጋ መንፈስ ቅዱስን የምናገኘው በእምነታችን ጸንተን በቤተ ክርስቲያን የሚፈጸሙትን ልዩ ልዩ ምሥጢራት በመቀበል እንደሆነ እን ረዳለን። ጸጋ መንፈስ ቅዱስም በክርስቶስ ለተሰጠን ተስፋችንና ለዘላለም ርስታችን መያዣ (ዐረቦን) ነው (2ኛ ቆሮ.1፥20-22፤ ኤፌ.1፥11-14)።

እንግዲህ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በምሥጢራት ባገኘነው ጸጋ ተነሣስተን ለጸሎት እንተጋለን። ይልቁንም ዘወትር የአቡነ ዘበሰማያትን ጸሎት በማድረስ ከእምነታችን፥ ከተስፋችንና ከፍቅራችን ባለቤት ከሆነው ከእግዚአ ብሔር ጋር በመንፈስና በእውነት በመገናኘት የተስፋችንን ቃል ኪዳን እናጠናክራለን። በተስፋውም እየተደሰትን፥ ፈተናና መከራን እየታገሥን፥ የሚገባንን ለመሥራት፥ በፍቅሩም ሆነን መልካሙን ሥራ ለማከናወንና ዘወትር ለመታገል የሚያበቃንን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ እርሱ ባለቤቱ እን ዲጨምርልን እንደፈቃዱ እየኖርን በተአምኖ ብንለምነው አይነሣንም።

<u>የጌታ ክህነትና የማዳን ሥራው በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ይቀጥላል</u>

ለጸሎትና ወንጌልን ለማስተማር ከመትጋታቸው ጋር ሐዋርያት ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ይፈጽሙ እንደ ነበር ተገልጿል። ይህም ማለት በየጊዜው ያጠምቁና ያቆርቡ ነበር ማለት ነው (የሐዋ.ሥራ 2፥38-42)። ጌታ የማዳን ሥራውን የፈጸመው እንደ መሥዋዕትና እንደ ሊቀ ካህናት በመሆኑ ስለ ነበር ሐዋርያትም የርሱን መሥዋዕት በማቅረብ የእርሱን የክህነት ሥልጣን ወክሎ በመሥራት የማዳን ጸጋውን ለብዙዎች አዳርሰዋል። ዛሬም ይህንን ሥራ በመቀጠል ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን ከመስበክ ጋር ሲወርድ ሲዋረድ በመጣላት የክርስቶስ የክህነት ሥልጣን መሠረት የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ጸጋ በክርስቶስ ስም ላመኑት ሁሉ ለማዳረስ ትጥራለች።

ኃጢአትን እንድታስተሠርይ ጌታ በሰጣት ሥልጣን "በስሙም ንስ ሐና የኃጢአት ሥርየትን" በመስበክና ልዩ ልዩ ምሥጢራትን በመፈጸም ተነሳ ሕያንን ከኃጢአት እሥራት በመፍታት ቤተ ክርስቲያን ሰውን ከእግዚአብሔር ታስታርቃለች፥ ሰውና ሰውንም በፍቅር ታስተባብራለች (ዮሐ.20፥21-23፤ ሉቃ.24፥47)። "የማስታረቅም አገልግሎት" ለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ካህ ናት ተሰጥቷል። በሐዲስ ተፈጥሮ "የሆነው ሁሉ፥ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስ ታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን፥ ከእግዚአብሔር ነው፤ እግዚአ ብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለመን ከእርሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፥ በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ። እን ግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማለድ ስለ ክርስቶስ መልዕክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን። . . ." ይህንን ቃል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለራሱና ለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች በተ ሰጠው ሥልጣን መሠረት ተናግሮታል (2ኛ ቆሮ.5፥18-21)። የማስታረቁና የማዳን ሥራው እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ እንዲቀጥል ጌታ ለሐዋርያቱና ለተተ ኪዎቻቸው በጸጋ መንፈስ ቅዱስ የክህነትን ሥልጣን ሰጥቷቸዋል። ምክንያቱም በእነርሱ በሚፈጸመው ምሥጢራት፥ በጸሎትና በቃሉ አገል ግሎት አማካይነት የመዳን ጸጋ ለዓለም ሁሉ እንዲዳረስ ነው።

www.eotc-mkidusan.org

ለ) ስለ ጸጋና ስለ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን

1. የጸጋ ትርጉም -- ምንነቱና ዓይነቱ

ጸጋ ምን ማለት እንደሆነ ከማየታችን በፊት ጸጋ ከየት መጣ? በማን በኩል መጣ? የሚለውን በመመልከት እንጀምራለን፡፡ የኦሪት ሕግ በሙሴ በኩል እንደ መጣልን ጸጋን ደግሞ በክርስቶስ እንዳገኘን በዮሐንስ ወንጌል ተጽፏል፡፡ እንዲህም ተብሏል "ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበርና ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ፡፡" ይህም ማለት ጸጋ እግዚአብሔር በምሥጢረ ሥጋዌ በክርስቶስ ሰው መሆን የተገኘ ነው ማለት ነው፡፡

ስለዚህም "ቃል ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ÷ . . . እኛ ሁላችን ከሙላቱ ተቀብለን በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናልና" በማለት ወንጌላዊ ዮሐንስ የጸጋን ነገር ገልጸልናል፡፡ እንግዲህ ጸጋ በክርስቶስ ሰው መሆን የተገኘና በእርሱ ላመኑት ሁሉ በነፃ የሚሰጥ ነው፡፡ ጸጋ በአጠቃላይ አነጋገር እግዚአብሔር ዓለሙን እንዲሁ ከመውደዱ የተነሣ አንድ ልጁን ለዓለም መድኃኒት አድርጐ መስጠቱን የገለጸበት የፍቅሩና የምሕረቱ የሥራ ውጤት ነው (ዮሐ.1÷12-18፤ 3÷16፤ 1ኛዮሐ.4÷7-12)፡፡ በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ በሙሴ ሕግ በኩል ሳይሆን በክርስቶስ ጸጋ በመምጣቱ ያመኑትን እንዲሁ አጽድቋቸዋል (ሮሜ.3÷21-26)፡፡ እንግዲህ የጸጋ መነሻ ምንጩ ከእግዚአብሔር ፍቅርና ከማዳን ሥራው ነው፤ በተለይም ለእኛ ሲል ሕማምና ሞትን ከተቀበለልን ከክርስቶስ ሥጋና ደም ነው፡፡

በሙሴ በኩል የመጣው ሕግ ይህን አድርግ ይህን አታድርግ በማለት ልናደርገው የሚገባንና የማይገባንን ለይቶ የሃይማኖት፥ የሞራልና የማኅበራዊ ግዴታችንን የሚያስታውቀንና እንድንፈጽምም የሚያስገድደን ትእዛዝ ነው፡፡ ትእዛዙን ባንፈጽም ግን ቃል ኪዳኑን እንዳፈረሰን ተቆጥሮ እስከ ሞት የሚደርስ ቅጣት ይፈረድብናል፡፡ የሙሴን ሕግ የጠበቀና ያከበረ በሕይወት እንደሚኖር ተነግሯል፡፡ ነገር ግን በታሪክ እንደምናየው ማንም ሕጉን ጠብቆ ከሞት ፍርድ የዳነ የለም፡፡ የመጀመሪያው ትእዛዝ ለአዳም ተሰጥቶ ነበር፡፡ ነገር ግን ትእዛዙን በማፍረሱ የሞት ሞት ተፈረደበት፡፡

የሙሴንም ሕግ በትክክል የፈጸመ ባለመኖሩ ሰው ሁሉ ከሞት ፍርድ አላመለጠም፡፡ ምክንያቱም ሁሉ ስለ በደለ ነው፡፡ "ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ፤ አስተዋይም የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፤ ሁሉ ተሳስተዋል÷ በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል፤ ቸርነት የሚያደርግ የለም÷ አንድ ስንኳ የለም፡፡" ብሎ ሐዋርያው ጳውሎስ መዝሙረ ዳዊትን ጠቅሶ ያስተማረንን እናስተውላለን (ሮሜ.3÷11-12)፡፡ ስለዚህ በሙሴ ሕግ ማንም ሊጸድቅ አልቻለም፡፡ ምክንያቱም ሕግ ሰውን ከኃጢአቱ ለማላቀቅ ችሎታና ኃይል ስለሌለው ነው፡፡ እንዲያውም የሕግ መኖር ኃጢአትን አላገደም÷ ሕግ መተላለፍ እየበዛ÷ የኃጢአትም ምንነት እየጐላና እየታወቀ ሄደ እንጂ (ሮሜ.7÷7-12)፡፡

በክርስቶስ የተገኘው ጸጋ ግን ኃጢአትን የሚደመስስ÷ሰውን ከእግዚአብሔር የሚያስታርቅ÷ መንግሥተ ሰማያትን የሚያሰጥ ሆኗል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደዚህ ዓለም ልኮ ለሰዎች ሁሉ ቤዛ አዳኝ አድርጎ በመስጠቱ የመዳን ጸጋችንን አገኘን፡፡ ስለዚህ ሕፃን ተወለደልን ወንድ ልጅም ተሰጠን በማለት ኢሳይያስ የተነበየው በክርስቶስ መወለድ ጸጋችንን ማግኘታችንን ይገልጻል፡፡ "ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና" የሚለው

www.eotc-mkidusan.org

ቃል ስጠታን ማለት የጸጋ ስጦታን ያመለክታል (ኢሳ.9፥6)፡፡ ስለ እኛ ስለ መዳናችንም ሰው የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ በሰውነቱ የሕግን ቀንበር ተሸክሞ ስለ እኛ ትእዛዛትን ሁሉ ፈጽሟል፡፡ በዚህም ሕግን በፈጸመው ሰውነቱ ሕግን ባለመፈጸማችን የተፈረደብንን የሞት ቅጣት በእኛ ምትክ ተቀብሎ አድኖናል፡፡ ጸጋም በእርሱ ሞት ያገኘነውን የዘላለም ሕይወት ይመለከታል፡፡

ስለዚህ ስለ ሥጋ ድክመት ሕግን ለመፈጸም ባለመቻላችን ያጣነውን ሕይወት በክርስቶስ ሕማማትና ሞት አገኘነው፡፡ በእርሱም በማመናችን እና ደፈቃዱም በእርሱ መንፈስ በመመላለሳችን ሕግንና ትእዛዛትን ሁሉ እን ደፈጸምን ተቆጥረናል፡፡ ስለዚህም በክርስቶስ ላለነው ሁሉ ኩነኔ እንደሌለብን ተጽፏል (ሮሜ.8፥1-4)፡፡ እንግዲህ ከክርስቶስ ሰውነት በመስቀል ላይ በፈሰሰው ደሙ የተገኘው ጸጋ ዓለምን ሁሉ ከኃጢአትና ከሞት ፍርድ ያድናል፡፡ የዘላለምን ሕይወት ያስገኛል፡፡ በኃጢአት የሞት ጥላ ሥር ላሉ ሁሉ ከዚህ የበለጠ የሕይወት ጸጋ የት ይገኛል? የብርሃን ሕይወትስ የት አለ?

ጸጋ ምንድን ነው? ዓይነቱስ?

እንግዲህ ጸጋ ምን ማለት ነው? ጸጋን ከመሠረቱ ልንረዳው የምን ችለው እኛን ለማዳን ሲል ክርስቶስ ሰው በመሆኑ፥ በሕማመ-ና በሞቱ ምክን ያት ኃጢአትን ደምስሶ ሰውን ከእግዚአብሔር በማስታረቁ ነው፡፡ ይህም ማለት የጸጋ የመጀመሪያ ዓላማና የሥራ ውጤት የአዳምንና የልጆቹን በደል መደምሰስና ከፈጣሪም ይቅርታን ማስገኘት ነው፡፡ "እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ" በማለት ዮሐንስ መጥምቁ ስለ ክርስቶስ መስክሯል (ዮሐ.1፥29)፡፡ "ወደሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያነጽሐነ እምኵሉ ኃጣውኢነ - የኢየሱስ ክርስቶስም ደም ከኃጢአታችን ሁሉ ያ ነጻናል" (1ኛዮሐ.1፥7)፡፡ ስለሰዎች ኃጢአት የተሠዋው በጉ፥ የፈሰሰው ደሙ ለኃጢአተኞች ሁሉ ፈውስ፥መድኃኒት ሆኗል፡፡ ጸጋ ማለትም ይህ ነው፡፡ ስለዚህ ነው የክርስቶስ ሥጋና ደም በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከፍተኛ ክብር የሚሰጠው፡፡ ስለዚህም ምሥጢረ ቁርባን የምሥጢራት ሁሉ መሠረትና የጸጋ ሁሉ መገኛ ሆኗል፡፡ ምክንያቱም የደኅንታችን ጸጋ በመስቀል ላይ ከተሠዋው ከክርስቶስ ሥጋና እንዲሁም ከፈሰሰው ደምና ውኃ የተገኘ ነውና፡፡

እንግዲህ ጸጋ ማለት በመጀመሪያ ደረጃ በክርስቶስ ቤዛነት ከእግዚአ ብሔር የሚገኝ የኃጢአት ሥርየትና እርቅ ነው፡፡ ፍጡር ከፈጣሪ መታረቅ የመጀመሪያ የጸጋ ውጤት ነው፡፡ የጠፋው ልጅ ከአባቱ ጋር የመታረቁን ታሪክ እዚህ ላይ እናስታውስ (ሉቃ.15፥11-24)፡፡ ክርስቶስ በጸጋው እንዳጸደቀን፥ እርቅና ሰላምን እንደሰጠን፥ ኃጢአት ባለበትም እንዴት ጸጋውን እንዳበዛልን እንመልከት (ሮሜ.5፥1-31)፡፡

ጸጋ የኃጢአት መደምሰሻ ነው ስንል በዚህ ብቻ የሚቆም አይደ ለም፡፡ ጸጋ ኃጢአትን ከደመሰሰ በኋላ በኃጢአት ምክንያት የመጣውንም ሞት ያስወግደዋል፡፡ በክርስቶስ ሕማምና ሞት የተገኘው ጸጋ የዘላለም ሕይወትን ያስገኛል፥ ገነት መንግሥተ ሰማያትን ያሰጣል፡፡ ስለዚህ ጸጋ ከሁሉ ነገር በላይ ነው፡፡ ምክንያቱም ጸጋ የእግዚአብሔር ፍቅር የሚገለጽበት የቸርነቱና የምሕረቱ ውጤት ነውና፡፡

እንግዲህ በሁለተኛ ደረጃ በጥንተ አብሶ በአዳም ኃጢአት፥ ሕግ በማፍረሱ ምክንያት የመጣብንን መርገም ሽሮ ሞትን ደምስሶ በክርስቶስ የተገኘው ጸጋ የዘላለም ሕይወትን አሰጥቶናል፥ ያጣነውን ገነት አስመ

www.eotc-mkidusan.org

ልሶልናል፡፡ ስለዚህ ጸጋ ማለት ጽድቅንና መዳንን ለማግኘት የሚረዳን ከእግዚአ ብሔር የሚገኝ ስጦታ ነው፡፡ በጸጋው አዲስ ሕይወትን አግኝተን አዲስ ፍጥረት ሆነናል፡፡ ጸጋ የእግዚአብሔር ልጅነትን አስሰጥቶ የመንግሥቱ ወራሽ አድርጉ የመጨረሻውን ተስፋና ደስታ ለመካፈል ያበቃናል (2ኛቆሮ.5÷17፤ ኤፌ.1÷5-8፤ 2÷5-10፤ ገላ.6÷15፤ ሮሜ.8÷14-17)፡፡

በዚህና በመሳሰሉት ልዩ ልዩ የጸጋ ትርጓሜ ለመገንዘብና ለማስገንዘብ የምንፈልገው ነገር ቢኖር ጌታ አምላክ ከሰው ልጅ የሚያገኘው ጥቅም ሳይኖር እንዲያውም የፈጣሪውን ቃል ኪዳን ተላልፎ በመበደሉ የእግዚአብሔር ጠላቱ ሆኖ ሳለ (ሮሜ. 5÷6-11) እርሱ ግን በዓይነ ምሕረት ተመልክቶ ታላቅ የቸር ነትና የርኅራኄ ሥራ ማድረጉ ለሰው ልጅ ያለው ፍቅር ምን ያህል ታላቅ እን ደሆነ በአድናቆት እንድንመለከተው ነው፡፡ "በልዎ ለእግዚአብሔር ግሩም ግብርከ- እግዚአብሔርን ሥራህ ግሩም ነው በሉት" (መዝ.65÷3) እያልን ታላቁን የፍቅር ሥራውን በአንክሮና በተዘክሮ ሆነን እንማረዋለን፡፡ እንግዲህ ይህ እጅግ የሚያስደንቀው አምላካዊ የፍቅር ሥራው ሁሉ ጸጋ ይባላል፤ እግዚአ ብሔር ለሰው ልጅ እንዲሁ በነፃ ያደረገለት የረድኤት ሥራ ነውና፡፡ ጸጋንም ጸጋ ያሰኘው ከቸሩ እግዚአብሔር ያለምንም ዋጋ ለሰዎች ደኅንነት በነፃ የሚሰጥ ስለሆነ ነው፡፡ ከኃጢአትና ከሞት ድነን ከመንፈሳዊ ልደት እስከ ዘላለማዊ ሕይወት እስከ መንግሥተ ሰማያት ድረስ በነፍስ በሥጋ የሚደረግልን ረድኤተ እግዚአብሔር ሁሉ ጸጋ ማለት እንደሆነ እናምናለን፡፡ እንግዲህ ስለነዚህ የጸጋ ስጦታዎች ሁሉ ምን እናድርግ ብለን እናስባለን፡፡ በመዝሙረ ዳዊት "ምንተ ኑ አዐሰዮ ለእግዚአብሔር በእንተ ኵሉ ዘገብረ ሊተ- ለእግዚአብሔር ስላደረገልኝ ሁሉ ምንን እከፍለዋለሁ" (መዝ. 115÷3) እንደተባለው ከምስጋና ሁሉ የሚበልጠውን የምስጋና መሥዋዕት ለእርሱ ብቻ ከማቅረብ በቀር ሌላ ምን እናደርጋለን፡፡ ምስጋና የባሕርዩ ለሆነ አምላክ በእውነት ምስጋና ይገባዋል፡፡

ስለ እግዚአብሔር የጸጋ ስጦታዎች በብዙ መንገድ መተርጐማቸውን እያሰብን ዓይነታቸውንና ብዛታቸውን በጽሑፍ ወይም በሰንጠረዥ ዘርዝሮ ለማሳ የት አይደለም፡፡ እንዲያው በክርስቶስ ያመኑ ሁሉ ጸጋ በጸጋ እንደሆኑና ጸጋም በእጅጉ እንደበዛላቸው ለማስገንዘብ ያህል ነው እንጂ፡፡ በክርስቶስ የመጣልን ጸጋ በጥንተ ተፈጥሮ የወደቀውን ሰው በሐዲስ ተፈጥሮ አድኖ የመጨረሻ ዕድል ፋንታውን ከእግዚአብሔርና ከቅዱሳኑ ጋር እንዲሆን አብቅቶታል፤ በመርገመ ሥጋና በመርገመ ነፍስ ፋንታ በረከተ ሥጋና በረከተ ነፍስን ሰጥቶታል ብለን ለመመስከር ያህል ይህን አጭር የጸጋ ትርጓሜ ለማሳየት ሞክረናል፡፡

ከሞላ ጐደል የጸጋ ትርጉም ይኸን ሲመስል በክርስቶስ የመጣውን የጸጋ ስጦታ ሁሉ በእምነትና በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ለመቀበል እንድን ችል የሚያበቃንን መንፈስ ቅዱስን መዘንጋት የለብንም፡፡ የክርስቶስን ጸጋ ለመቀበላችንም ሆነ ከተቀበልንም በኋላ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ረድኤት ያስፈልገናል፡፡ በጥምቀት ከክርስቶስ ጋር አንድ የሚያደርገንና የሞቱና የትንሣኤ ውም ተካፋይ የምንሆንበትን ሁኔታ በልቡናችን እንድንረዳውና በተግባርም እን ድንፈጽመው ያስችለናል፡፡

ክርስቶስን ጌታ እንደሆነ ያለ መንፈስ ቅዱስ ለመመስከር እን ደማንችል ሐዋርያው ጳውሎስ አስተምሮናል (1ኛቆሮ.12÷3)፡፡ ይህን ካልመሰከርን ደግሞ በክርስቶስ የመጣልንን ጸጋ ለማግኘት ይቅርና ገና በአ መክሮ እንዳሉትና እንዳልተጠመቁት ንዑሰ ክርስቲያን እንኳ ለመሆን አን ችልም፡፡ ስለዚህ የጸጋን ትርጉም በትክክል የምንገነዘበውና የጸጋንም ስጦታ ለመቀበል የምንችለው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት እንደሆነ እንረዳለን፡፡ እንግዲህ "ጸጋ እግዚአብሔር" ማለት ከሁሉ አስቀድሞ ራሱ መንፈስ

ቅዱስ ነው፡፡ እርሱም በመጀመሪያ ሥራው ሰውን በሀብት ስቦ በረድኤት አ ቅርቦ ወደ እግዚአብሔር በንስሐ መልሶ በክርስቶስ ማመንን ይሰጠዋል (ዮሐ.6፥37 እና 44-45)፡፡ የክርስቶስን የማዳን ጸጋውን፥ ጽድቁንና ቅድስናውን ሁሉ ገንዘብ ለማድረግ ማለት የራሳችን ሊሆን የሚችለው ከእግዚአብሔር በተ ሰጠን በልቡናችን ውስጥ ባደረው በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ረድኤት ነው፡፡ በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው ልዩ ልዩ ጸጋ ሁሉ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ይከናወናል፡፡ ከዚህም ሌላ በአማኞች ልቡና አድሮ መንፈስ ቅዱስ መልካ ም ሥራዎችን እንዲያከናውኑ ልዩ ልዩ ጸጋና ሀብት ያድላቸዋል፤ ለእያንዳን ዱም እንደሚገባውና እንደሚጠቅመው አውቆ "ከመከፈልታተ ሱታፌ ሀብት" እና "ከመከፈልታተ ምግባር" የሚያስፈልገውን ይሰጠዋል፤ ይህንንም የሚያደርገው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እምነት፥ ተስፋና ፍቅር እንዲጸና የእግዚአብሔር ወንጌል መንግሥት እንዲሰፋፋ ነው (1ኛቆሮ.12፤ ሮሜ.12፥6-8 ትርጓሜውን ተመልከት)፡፡

2. ጸጋው ከኃጢአትና በሕግም ከመኰነን ያድነናል

የኃጢአት ፍዳ

የጸጋን ታላቅነትና ምንነት በይበልጥ ለመገንዘብ የሚቻለው በቅድሚያ ኃጢአት በሰው ላይ ያለውን የአፍራሽነት ኃይልና የጥፋት ውጤት እንደዚሁም የሕግን የሥራ ድርሻ በመመልከት ነው፡፡ በመጀመሪያ ኃጢአት በአዳም ምክን ያት ወደዚህ ዓለም ሲገባ፥ ኃጢአት በእርሱ ላይ ብቻ እንዳልቀረና ወደ ልጆቹም እንደ ተላለፈ እንማራለን (ሮሜ.5፥12)፡፡ ቅንዓትና ነፍስ መግደልም በአዳም ልጆችና በቤተሰቡ ላይ ደረሰበት፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኃጢአት እየተስፋፋና እየተጠናከረ ሄደ፤ ዓለም የነፍሰ ገዳዮች ሆነች፥ ክፋትና ድን ቁርና፥ ርኵሰትና ዓመፅ በሰዎች ልቡና ነገሠ፡፡

በዚህም የተነሣ ፈጣሪ ሰዎችን በመፍጠሩ እስከ መፀፀት ደረሰ፡፡ በኖኅ ዘመን የነበሩትን የጥንት ሰዎችን /ሰብአ ትካትን/ ከጥቂቶች በስተቀር ምድርን ባጥለቀለቀው የጥፋት ውኃ አጠፋቸው፡፡ ከዚህም ታሪክ የኃጢአት ውጤት ምን እንደሚያስከትል እናስተውላለን፡፡ በሥጋም በነፍስም ሥቃይንና መከራን፥ ፍዳና ሞትን የሚያመጣብን እርሱ ብቻ ነው፡፡ ገነትን ያስዘጋ፥ ዓለምን በጥፋት ውኃ ያስደመሰሰ ሰዶምና ገሞራን በእሳት የአስቃጠለ እርሱ ምንድን ነው? ከአዳም የወረስነው እኛም የምንሠራው ያው ኃጢአት አይደለምን? ኃጢአት በሰው የክፋት እውቀትና ሥራ የተገነባና ከመሬት ወደሰማይ የወጣ እንደ ሰናዖር ሕንፃ እንደባቢሎን ግንብ የጸና ነው፡፡ እግዚአብሔር በቸርነቱ ባይገድበው ኖሮ የሰው ዘር ሁሉ ባልተረፈም ነበር (ዘፍ.6፥1-14፤ 11፥1-9፤ ኢሳ.1፥9)፡፡

የሕግ ኵናኔነት

የሕግ መታወጅ የትእዛዛት ብዛት ኃጢአትን አልቀነሰም በደልንም አላ ገደም፡፡ ከሕግ በፊት ክፉ ነገርን የሚከለክል በይፋ የወጣ ድንጋጌ ስለሌለ ሰዎች ኃጢአትን ሳያውቁ ይፈጽሙት ነበር፤ ከሕግ በኋላ ግን እያወቁ የሚያጠፉ ሆነዋል፡፡ ስለዚህም በሰው ሕይወት ውስጥ ኃጢአት በይበልጥ እየታወቀና እየተጠናከረ ከመሄዱ ሌላ ሕግ መተላለፉ፥ ቃል ኪዳን ማፍረሱ ተጨማሪ ጥፋት ስለሆነ የኀሊና ወቀሳና የሞራል ውድቀትን አስከትሏል፡፡ "በሕግ ባይሆን ኃጢአትን ባላወቅሁም ነበር" በማለት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የሕግንና የኃጢአትን ሁኔታ ያስተምረናል፡፡ "ሕጉ፡ አትመኝ ባላለ ምኞትን ባላወቅሁም ነበርና፡፡ ኃጢአት ግን ምክንያት አግኝቶ ምኞትን ሁሉ በትእዛዝ ሠራብኝ፤ ኃጢአት ያለ ሕግ ምውት ነውና፡፡ እኔም ዱሮ ያለ ሕግ ሕያው

ነበርሁ፤ ትእዛዝ በመጣች ጊዜ ግን ኃጢአት ሕያው ሆነ እኔም ሞትሁ፤" በማለት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የሚያስረዳን ሕግ በደልን እየቆጠረና እየመዘገበ በደለኛውን በፍርድ ይቀጣል፥ በሥጋም በነፍስም ይፈርዳል እንጂ የሰው ልጅ ላጋጠመው የኃጢአት መከራና ችግር መፍትሔ እንደማይሰጠው ነው (ሮሜ.7፥7-12)።

ሕግ እንደ መስተዋት ሆኖ በውስጣችን የሚገኘውን የኃጢአት እድፍና ጉድፍ ያሳየናል፤ እንድናስወግደውም ያዘናል እንጂ ሕጉ ራሱ አያስወግድልን ም። እንዲያውም ለንዑሳን ኃጢአትም ሳይቀር ይኰንነናል ይፈርድብናል እንጂ አ ይምረንም። ሁሉ ሰው ደግሞ የሕግን ትእዛዝና መመሪያ ተከትሎ በራሱ ትግል ብቻ ኃጢአትን ሁሉ ለመቋቋም እንደማይችል የታወቀ ነው። በሰውነታችን በተፈጥሮ አባሎቻችን ውስጥ የሚገኘው ሕገ ኃጢአት በኀሊናችን ውስጥ የሚገኘውን ሕገ እግዚአብሔር እንደምን እንደሚዋጋውና በመጨረሻም ሰው የኃጢአት ምርኮኛ እንደሆነ ከሕይወታችን፥ ከመንፈሳዊ ተጋድሏችንና ከምናየው የአኗኗር ልምድ ለመማር እንችላለን። የሥጋን ድክመት፥የኃጢአትን ገዢነት፥ የሰውን የተፈጥሮ ባሕርይ የተረዳው ሐዋርያው ጳውሎስ፦

> "በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር አውቃለሁና፤ ፈቃድ አለኝና፥ መልካ ሙን ግን ማድረግ የለኝም። የማልወደውን ክፉን ነገር አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን በጎውን ነገር አላደርገውም። የማልወደውን የማደርግ ከሆንኩ ግን ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም፥ በእኔ የሚኖር ኃጢአት ነው እንጂ።
> "እንግዲያስ መልካሙን አደርግ ዘንድ ስወድ በእኔ ክፉ እንዲያድብኝ ሕግን አገ ኝለሁ። በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛልና፥ ነገር ግን በብል ቶቼ ከአእምሮዬ ሕግ ጋር የሚዋጋውንና በብልቶቼ ባለ በኃጢአት ሕግ የሚማርከኝን ሌላ ሕግ አያለሁ። እኔ ምንኛ ጕስቁላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?" በማለት የብዙዎችን ጥያቄ ያስተጋባል። ለዚህም መልሱ በክርስቶስ ያገኘነው የማዳን ጸጋ ብቻ ነው በማለት እምነታችንን እንገልጻለን። ስለዚህ "በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን" (ሮሜ.7፥18-25)።

እንግዲህ መዳናችን በጸጋ ከሆነ ሕግ ምን ያስፈልጋል? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። በመጀመሪያ በሰው ልቡናና በሰዎች መካከል ስለሚገኘው ኃጢአትና ክፉ ነገር ሁሉ ለመረዳት የቻልነው በሕግ አስተማሪነት ነው። ይህም ማለት ከክፉው እንድንርቅ መልካሙንም እንድናደርግ ያስተምረናል ማለት ነው። ሁለተኛው በኃጢአትና በርኩሰት የምንኖር ከሆነ ከተቀደሰው ፈጣሪያችን ጋር አንድነትና ሰላም ሊኖረን እንደማይቻል ሕግ ይገልጽልናል። ሦስተኛው ሥጋ ለባሽ ሁሉ በሕግ ፊት ደካማና በደለኛ መሆኑን በማስታወቅ የእግዚአ ብሔርን ምሕረት እንዲጠይቅ ያደርገዋል። ምክንያቱም ሕግ ዓመፀኛውንም ሳይ ከሰውና ሳይፈርድበት አይተወውምና። ስለዚህ በትዕቢቱ ተዋርዶ ከሚጠፋ ይልቅ በትኅትና ሆኖ የእግዚአብሔርን የምሕረት መንገድ እንዲፈልግ ሕግ ሰውን በማስተማሩ በሕግ ሥር ያሉትን ሁሉ በጸጋው ሥር እንዲሆኑ ያዘጋጃ ቸዋል።

ጸጋም ከመጣ በኋላ በጸጋው ሥር ሆነን ሕግን እንድንጠብቅ እንጂ ሕግን እንድንሽረው የጸጋ ባለቤት ክርስቶስ አላዘዘንም (ማቴ.5፥17-20)። ሐዋርያው ጳውሎስም ሕግን እንድናጸናው እንጂ ሕግን እንድንተወው አላስ ተማረንም (ሮሜ.3፥31)። እንዲያውም ሕግ በጸጋ ሥር ላሉትና ለዳኑት ሁሉ ከሥነ ምግባር መመሪያነቱ በላይ "የዘላለምን ሕይወት" ለማግኘት አስፈላጊነቱ በወንጌል የተመሰከረ ነው (ማቴ.19፥16-19)። (በክፍል ሦስት ስለ ሕግና እን ዲሁም ስለ ጸጋ እንመለከታለን)

የጸጋ አዳኝነት

የክርስቶስ ጸጋ ከመሰጠቱ በፊት ሰው ሁሉ በራሱ ጥረት ሕግን ለመፈጸም ግዴታው ነበር፡፡ በዚህም የተነሣ የሕግን ትእዛዛት ሁሉ ለመፈጸም አዳጋች ስለሆነ ማለት አንዲቱን ትእዛዝ እንኳ የሻረ ሕግን ሁሉ እን ደተላለፈ ስለሚቆጠር ሁሉም በሕግ አፍራሽነት ተከሶ በሞት፥በሲኦል ይቀጣ ነበር፡፡ ከክርስቶስ በኋላ ግን ሕግን ሁሉ በፈጸመው በክርስቶስ ያመኑ በመንፈሱ የሚመሩ ሁሉ በእርሱ ጸጋ እንደ ሕግ ፈጻሚዎች ተቆጥረዋል (ሮሜ.8፥1-4)፡፡ እንግዲህ ክርስቲያኖች በእምነትም በሥራም በክርስቶስ ጸጋ ሥር ናቸው እንጂ ጸጋውን እንደ ተቃወሙት አይሁድ በሙሴ ሕግ ሥር አይደሉም፡፡ በጸጋው ሥር ሆነው ትእዛዛትን ሁሉ በሕገ ተፋቅሮ ፈጽመውታልና፡፡ ስለዚህም በበደላቸው የተነሣ በሕግ ከሳሺነት ከሚመጣው የሞት ፍርድ ነፃ ናቸው፡፡ ምክን ያቱም በክርስቶስ እምነትና ጥምቀት በተገኘው ጸጋ አማካኝነት ከበደላቸውና ከኃጢአታቸው የሚነጹበት፥ ምሕረት የሚያገኙበት የመዳን ጸጋ ስላላቸው ነው፡፡

ስለሆነም እውነተኛ አማኞች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንቅፋት ቢያጋጥማቸው ተስፋ አይቆርጡም፡፡ እንዲያውም ንሥሐ በመግባታቸው ጸጋ ይጨመርላቸዋል፡፡ መንፈሳዊ ተጋድሏቸውም ይጸናላቸዋል፡፡ ከበፊቱ ይልቅ የሕግ ትእዛዛትን ለመፈጸም የሚያስችልና የሚያበረታታ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ረድኤት ይበዛላቸዋል፡፡ በክርስቶስ በእውነት ላመኑትና ለተከተሉት ሁሉ የጸጋው አጋዥነትና የጸጋው አዳኝነት አይለያቸውም፡፡

የጸጋ አዳኝነት ስንል የሰው ልጆችን መዳን ያመለክታል፡፡ ታዲያ ሰው መዳኑ ከምን ነገር ነው? ታምሞ ነበር ወይስ ሞቶ? ለሚለው ጥያቄ መልሱ በክፍል አንድ እንደተመለከትነው በእርግጥ ሰው በራሱ ጥፋት መከ ረኛ፥ታማሚና ሟች መሆኑ ከአዳም ጀምሮ የነበረ ታሪክ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የሰው ዘር ከጥንተ አብሶ ጀምሮ ለፈጣሪው ሕግ ባለመታዘዙ በነፍስም በሥጋም ጐስቋላ ፍጡር፥ሕመምተኛና ሟች ሆኗል፡፡ ስለሆነም ለዚህ ችግራችን መፍትሔና መድኃኒት አስፈልጐታል፡፡ ሕግ ለዚህ ችግር መፍትሔ አይሰጥም፤ ምክንያቱም ሕግ መፍረድና መቅጣት እንጂ ማዳን አይሆንለትምና፡፡ ሰው ከወደቀበት አዘቅት በራሱ ጥረትና ትግል ብቻ ለመውጣት ቢያስብና ቢሞክርም አልተከናወነለትም፡፡ ሰው ራሱን ለማጥፋት ሲችል ራሱን ለማዳን ግን አልቻለም፡፡

በጥንተ አብሶ ለፈጣሪው ባለመታዘዙ፥ ከእግዚአብሔርም በመራቁ የ ነበረው ኃይልና ችሎታ ተቀንሷል፡፡ እንግዲህ ሰው ከወደቀበት አዘቅት ሊወጣ የሚችለው በእግዚአብሔር እጅና ክንድ ብቻ ነው፡፡ ይህም የክርስቶስ ጸጋ ነው፡፡ የተጐሳቆለችው ነፍሱ፥ የወደቀችው ሰውነቱ፥ የጠፋችው ሕይወቱ በክርስቶስ ጸጋ ልትነሣና ልትድን ችላለች፡፡ በጸጋም ከፈጣሪዋ ጋር በመታረቋ ሕይወትን አግኝታ እንደገና ተወልዳ አዲስ ፍጥረት ሆናለች፡፡ የሞት ሞት ከተፈረደባት ከሲኦልና ከዘላለም ሥቃይ ነፃ ወጥታለች፡፡

እንግዲህ በክርስቶስ አምነው ከዚህ ዓለም በሞት ለሚለዩት ሁሉ በገ ነት በደስታ የመኖር ተስፋ አላቸው፡፡ ነገር ግን ለማያምኑትና የክርስቶስ ጸጋ ለሌላቸው የሲኦል ሥቃይ ይጠብቃቸዋል፡፡ የጸጋ አዳኝነት፥ ለሚያምኑት ብቻ የተሰጠ ነው፡፡ አማኞች ነፍሳቸው ብቻ ሳይሆን ሥጋቸውም ይድናል፡፡ በትን ሣኤ ዘለክብር ከነፍሳቸው ጋር በመዋሐድ መንግሥተ ሰማያትን ይወርሳልና፡፡ የጸጋ ማዳን ለነፍስም ለሥጋም ነውና፡፡

በክርስቶስ አምነን በጸጋው ለዳንን ሁሉ ደግሞ ታላቁን የእግዚአ

ብሔርን ጸጋ ለመዳናችን ማስረጃ፥ ለተስፋችንና ለርስታችን መያዣ የሆነውን መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል እንድንችል እርሱ ባለቤቱ አብቅቶናል (ኤፌ.1፥13-14)፡፡ በተለይም የሰማዩ አባታችንን በእውነት ለሚለምኑት ሁሉ መንፈስ ቅዱስን እንደሚሰጣቸው በወንጌል ተጽፏል (ሉቃ.11፥13)፡፡ "በተሰጠንም በመን ፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን" እንደ ፈሰሰ ማለት እንደ አደረ ከሐዋርያው ጳውሎስ እንማራለን (ሮሜ.5፥5)፡፡ ይህም መንፈስ ቅዱስ የሚያጸናንና የሚያጽናናን የሚያነጻንም የቅድስናንም ጸጋ የሚሰጠን እርሱ ነው፡፡

ክርስቲያኖች ሁሉ ያለ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ እስከ መጨረሻው ድረስ በትዕግሥት መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ሊመሩና የመዳን ጸጋቸውን ሊያገኙ የሕይወት አክሊላቸውንም ሊቀዳጁ አይችሉም፡፡ በክርስቶስ ሕማምና ሞት የምሕረት ጸጋን፥ የኃጢአት ሥርየትን በእምነትና በጥምቀት አግኝተናል፡፡ ይህንንም ከክርስቶስ ያገኘነውን ጸጋ በልዩ ልዩ ፈተና ምክንያት እንዳንተወውና እንደገናም ከከፍተኛ የኃጢአት አዘቅት ውስጥ እንዳንወድቅ የሚረዳን መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ በቅድስና ጕዳና የሚመራንና ከክፋትና ከነውር ሥራ ሁሉ እንድን ርቅ፥ በመልካም አኗኗር ራሳችንን እንድንቆጣጠርና በፍቅረ እግዚአብሔር እን ድንያዝ ሊያደርገን የሚችል እርሱ ብቻ ነው፡፡

መንፈስ ቅዱስ ከቅድስና ጸጋው ጋር ለመዳናችን የሚያዘጋጁንንና የሚያስፈልጉትን ልዩ ልዩ ጸጋዎች ማለት ስጦታዎች በክርስቶስ ላመኑት ለቤተ ክርስቲያን አባላት ያድላል (1ቆሮ.12፥4-31)፡፡ ለአንዳንዶች የማስተማር ስጦ ታ፥ ለሌሎች ተአምራት የማድረግ፥ በልሳን የመናገር፥ ሰውን የመርዳትና የማስተዳደር አገልግሎት ይሰጣል፡፡ በነዚህና በሌሎችም ልዩ ልዩ ስጦታዎች ምክንያት ሕዝበ ክርስቲያኑ መንፈሳዊ ኑሯቸው እንዳይደክምና በሃይማኖትና በምግባር በትሩፋትም ጸንተው ለተስፋው ሀገር ለገነት ለመንግሥተ ሰማያት እን ዲበቁ ይሆናሉ፡፡ ምእመናን መሪያቸውን ክርስቶስን በእግር ሳይሆን በግብር እን ዲከተሉትና እርሱንም እንዲመስሉት የሚያበቃቸው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ነው፡፡ እንግዲህ መልካሙን ሥራ ለመሥራት ሐሳቡን የሚሰጠን፥ ፈቃዳችንንም የሚያ ነሣሣው የእግዚአብሔር ጸጋ መሆኑን አምነን ለመንፈስ ቅዱስ መታዘዝ ይኖርብናል፡፡ ስለዚህ "ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ" (ኤፌ.4፥30)፡፡

3. <u>የጸጋና የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ግንኙነት</u>

ስለ ጸጋ ከላይ ተመልክተናል፡፡ ከእንግዲህ ወዲህ ጸጋ ከምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያለውን ግንኙነትና የምሥጢራትን ምንነት በታሪክና በምሳ ሌ ጭምር እንደሚከተለው በአጭሩ እንመለከታለን፡፡ በእግዚአብሔር ጸጋ ማለት በመስቀል ላይ በፈሰሰው በክርስቶስ ደም የሰው ልጆች ኃጢአት ተደምስሶ ዓለም ሁሉ እንደዳነ እናምናለን፡፡ ይህ አንድ ጊዜ የተፈጸመው የማዳን ሥራና ጸጋው ለሁሉም ሰው የተሰጠ ቢሆንም ተቀባይ ከሌለ ደግሞ መሰጠቱ ብቻ በቂ አይሆን ም፡፡ ስለዚህ ጸጋን ለማግኘት አምኖ ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣት ያስፈልጋል፡፡ ጸጋ ላመኑትና ለተዘጋጁት ሁሉ በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አ ማካኝነት ይሰጣል፥ ይታደላል፡፡ እንግዲህ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የተባሉት የክርስቶስን ጸጋ በእምነት የምንቀበልባቸው የተቀደሱ የጸጋ ምልክቶችና መሣሪያዎች ሲሆኑ በማይታየው ውስጠ ምሥጢራቸው ደግሞ በቃለ እግዚአብሔርና በጸሎት አማካይነት ጸጋን የሚያስገኙና በግብረ መንፈስ ቅዱስ ለአማኞች የሚከፋፈሉ የጸጋ ስጦታዎችን የያዙ ናቸው፡፡ በዚህም የተነሣ ቤተ ክርስቲያን የጸጋው ግምጃ ቤት ተብላለች፡፡ ምክንያቱም በሚታየው ምሥጢራቷ አማካይነት የማይታየውን ጸጋ እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ መሠረት

በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ጠብቃና ይዛ የምትገኝና በየጊዜውም ጸጋውን የምታሰጥ በመሆኗ ነው።

ስለ ምሥጢረ ቤተ ክርስቲያን ምንነት ሲጽፉ የግብፁ ቄስ ማርቆስ ዳውድ እንደሚከተለው በአንድ ዓረፍተ ነገር ገልጸውታል፦ "ምሥጢረ ቤተ ክርስቲያን የተቀደሰ ሕግና ሥርዓት ነው፤ በእርሱም በኩል አማኝ ሁሉ በሚታይ ወይም በሚሰማ አኳኋን በአፍአዊ /በውጭ/ ምልክት [አማካይነት] የማይታየውን ጸጋ ይቀበላል"።[67]

ክርስቶስን ማመናችንና መቀበላችን የሚረጋገጠው፥ በጸጋው መዳናችንም የሚታወቀው ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን በመፈጸም ብቻ መሆኑን ማመን ይኖርብናል። አለበለዚያ ግን ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ሆኖ በግለኝነትና በራስ አስተያየት ብቻ ተመርቶ እግዚአብሔር ያውቃል፥ እርሱ ያድነኛል፥ ሌላው ነገር አያስፈልገኝም እያሉ የቤተ ክርስቲያንን ምሥጢራት በመናቅ፥ በክርስቶስ ወንጌል የታዘዙትን የጸጋ ምሥጢራት ሳይፈጽሙ መቅረት፥ የክርስቶስ ደም የተከፈለበትን ጸጋ ማክፋፋት ስለሆነ አዲሱን ኪዳን እንደአፈረሱ ተቆጥሮ በእግዚአብሔር ዘንድ ቅጣትን ያስከትልባቸዋል። ወደ ዕብራውያን በተጻፈው መልእክት እንደተገለጸው "የጸጋውን መንፈስ" የተቃወሙት አይሁዶች ከሁሉ የባሰ ቅጣት እንደሚገባቸው ያመለክታል።

> "የሙሴን ሕግ የናቀ ሰው ሁለት ወይም ሦስት ቢመሰክሩበት ያለ ርኅራኄ ይሞታል፤ የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደርኩስ ነገር የቆጠረ የጸጋውንም መንፈስ ያክፋፋ፥ እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል? . . . ደግሞም፦ ጌታ በሕዝቡ ይፈርዳል። በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ የሚያስፈራ ነው" (ዕብ.10፥28-31)

ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን በታሪክና በምሳሌ

ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን በማን በኩል ተሰጡ? ማንስ መሠረታቸው? ታሪኩና ምሳሌውስ እንዴት ነው? ለሚሉት ጥያቄዎች በአጭሩ እንመልሳለን። በሙሴ በኩል ለሕዝበ እሥራኤል የኦሪት ሕግ እንደተሰጣቸውና የብሉይ ኪዳን የመሥዋዕትና የቁርባን ፥ የጸሎትና የአምልኮት ሕግና ሥርዓት እንደ ተሠራላቸው እንዲሁም በክርስቶስ በኩል የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ለሕዝበ ክርስቲያን ተሰጥቷቸዋል፤ የሐዲስ ኪዳን መሥዋዕተ ቁርባንና የልዩ ልዩ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት ተሠርቶላቸዋል። ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንም በክርስቶስ እንደ ተመሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ፥ የቤተ ክርስቲያን ታሪክና የሐዋርያት ትውፊት ያስረዱናል። ለመዳናችንና ለመቀደሳችን ለክርስቲያናዊ ሕይወታችንም መሠረት የሆነን የክርስቶስ ጸጋ በመንፈስ ቅዱስ ለምእመናን ሁሉ የሚታደልባቸው ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሚባሉ አሉ። እነርሱም፦

(1) ምሥጢረ ጥምቀት
(2) ምሥጢረ ሜሮን
(3) ምሥጢረ ቁርባን
(4) ምሥጢረ ክህነት
(5) ምሥጢረ ተክሊል
(6) ምሥጢረ ንስሐ
(7) ምሥጢረ ቀንዲል ናቸው።

የመጀመሪያ ሦስቱን ምሥጢራት ሁሉም ሰው በቅድሚያ የሚቀበላቸው ሲሆን፥ እነርሱንም አለመቀበል የክርስቶስን ጸጋና በረከት አሳጥቶ በገሃነም

[67] Rev. Marcos Daoud, The Orthodox Church: Church Sacraments (Addis Abeba, Tinsae Zegoubae Printing Press, 1952) p. 3.

www.eotc-mkidusan.org

ለዘላለም ያስቀጣል፡፡ ምክንያቱም እነርሱን አለመቀበል ምሥጢረ ሥጋዌን እን ደ አለመቀበል ማለት ጌታ ሰው መሆኑን፥ ጥምቀቱን፥ ሕማማቱን፥ሞቱንና ትንሣኤውን እንደ መካድ ስለሚቆጠር ነው፡፡ ንስሐ ገብቶ በወንጌል ያመነና የተጠመቀ ግን ይድናል (ማር.1፥15፤ 16፥16)፡፡

በክርስቶስ ያገኘነው ነፃነትና አዲስ ሕይወት በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አማካይነት ለአማኞች ሁሉ ይሰጣል፡፡ የዚህንም ታሪክና ምሳሌ በአሪት መጻሕፍት ውስጥ እናገኘዋለን፤ እያነፃፀርንም እንማረዋለን፡፡ እሥራኤ ላውያን ደመ በበሩ መቃን ላይ በተረጨው በፋሲካ በግ ከመከራና ከሞት እን ደዳኑና ከግብፅ ባርነት ነፃ እንደወጡ፥ ክርስቲያኖችም በመስቀሉ ላይ በፈሰሰው የክርስቶስ ደም ከኃጢአትና ከሞት ድነዋል፥ ከዲያብሎስ ግዞትም ነፃ ወጥተዋል (ዘፀ.12፥21-51)፡፡ “ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዷልና” (1ኛቆሮ.5፥7)፡፡ ዛሬም ይህንን የደኅንነትና የነፃነትን ጸጋ መቀበላችንና ማግኘታችንን የምናረጋግጠው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚሠዋው በክርስቶስ ሥጋና ደም በቅዱስ ቁርባን መሥዋዕት ነው፡፡

እሥራኤላውያን በቀይ ባሕር ውስጥ በተአምራት ተሻግረው ነፃ ሕዝብ በመሆን አዲሱን የነፃነት ኑሮ እንደ ጀመሩ ሁሉ እንዲሁም ክርስቲያኖች በምሥጢረ ጥምቀት እንደገና ተወልደው አዲስ ፍጥረት ለመሆናቸው የሚያስረዳን ታሪክና ምሳሌ ነው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ “ሁሉም ሙሴን ይተባበሩት ዘንድ በደመናና በባሕር ተጠመቁ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መብል በሉ፥ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፤ ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ ድንጋይ ጠጥተዋልና፥ ያም ድንጋይ ክርስቶስ ነበረ” ያለውን ተመልከት (1ኛቆሮ.10፥1-4)፡፡ እንግዲህ ሕዝበ እሥራኤል ሙሴን የተባበሩት በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ከሆነ ሕዝበ ክርስቲያንም ከክርስቶስ ጋር ሊተባበሩ የሚችሉት በባሕሩ በተመሰለው በጥምቀት፥ በደመና በተመሰለው በምሥጢረ ሜሮን፥ በመንፈሳዊ ምግብና መጠጥ በተመሰለው በሥጋውና በደሙ ምሥጢር በመሳተፍ እንደሆ ነ እናምናለን፡፡ እነዚህ ሦስቱን ካልፈጸምን ከክርስቶስ ጋር ኅብረት አንድነት የለንም፡፡

በደብረ ሲና በእሳትና በመለከት ድምፅ ታጅቦ የታወጀው ሕገ ኦሪት ለቤተ እሥራኤል ሁሉ የሕይወታቸው መመሪያና መተዳዳሪያ እንደሆነ ሁሉ እንዲሁም በኢየሩሳሌም በጽርሐ ጽዮን በልሳነ እሳት በበዓለ ኀምሳ የወረደው መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያንን በጸጋውና በሕገ ተፋቅሮ የሚመራና የሚያስተዳድር ሆኗል፡፡ ወደሚያስፈራው የሲና ተራራ ሳይሆን አእላፍ መላእክትና የበኵራት ማኅበር በደስታ ወደ ተሰበሰቡበት የጽዮን ተራራ፥ የእግዚአብሔር ከተማ ወደ ሆነችው ሰማያዊት ኢየሩሳሌም በመንፈስ ቅዱስ አማ ካኝነት እንደርሳለን፡፡ ለዚህ የሚያበቃንን ጸጋ ከእርሱ እናገኛለን፡፡ ይህም የመን ፈስ ቅዱስ ጸጋ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለጥሙቃን በምሥጢረ ሜሮን የሚ ሰጠው የክርስቲያንን ሕይወት የሚያድሰውና የሚቀድሰው እንደሆነ እናምናለን (ዘጸአ.19-20፤ የሐዋ.2፥1-47፤ 8፥14-17፤ 19፥1-7፤ ዕብራ.12፥18-29)፡፡

እሥራኤላውያን ከተሰፋው ሀገር እስኪገቡ ድረስ በድንኳን ውስጥ ከበረሓ ወደ በረሓ አርባ ዓመት ሙሉ ሲንከራተቱ ከሰማይ የወረደ መና እየተመገቡ እንደኖሩ ሁሉ እንዲሁም ክርስቲያኖች በድንኳንና በበረሓ በተመሰሉት በሥጋ ድንኳናቸው (በሰውነታቸው) እና በዚህ ዓለም ኑሯቸው እስካሉ ድረስ ምግብ-ነፍስ የሚሆናቸውን ከሰማይ የወረደውን እውነተኛ የሕይወት ምግብ የክርስቶስን ሥጋና ደም በመመገብ ይኖራሉ (2ኛ ቆሮ.5፥1-9፤ ዮሐ.6፥48-51)፡፡ ስለዚህ ነው ዛሬ ምሥጢረ ቁርባንንና ቃለ እግዚአብሔርን በየጊዜው ማግኘት ያለብን፡፡

ክርስቲያኖች በዚህ ዓለም መጻተኞች እንግዶች ማለት ሀገር እን ደሌላቸው ተንከራታቾች ሆነው የሚኖሩበት ምክንያት እውነተኛ ሀገራቸው ገነት መንግሥተ ሰማያት ስለሆነች ነው፡፡ በእንደዚህ ያለ የችግር ኑሮ ውስጥ ሲኖሩ ሳለ በትዕግሥት እንዲወጡትና መከራውንም በመቻል በሰላም እን ዲያልፉት ለተሰፋውም ሀገር እንዲበቁ የሚያደርጋቸው በክርስቶስ የተገኘው የጸጋ እግዚአብሔር ረድኤት ነው፡፡ ጸጋ እግዚአብሔርም የሚገኘው በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ስለሆነ ከሥጋ ልደቱ ጀምሮ እስከ ሞቱ ድረስ ለመንፈሳዊ ልደቱና ለክርስቲያናዊ ሕይወቱ የሚያስፈልጉትን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ማናቸውም ክርስቲያን መቀበል ግዴታው ነው፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ ነቱን የቤተ ክርስቲያን አባልነቱን ሳያከብር የቀረ ግን ዕለት በዕለት የሚያስፈልገውንና ለክርስቲያናዊ ሕይወቱ የሚጠቅመውን መንፈሳዊ ምግብና ኃይል ስለማያገኝ በድካም ምክንያት ከመንገድ ላይ ወድቆ በመቅረት ከተሰፋው ሀገር አይደርስም፡፡

ጸጋ ከቤተ ክርስቲያን ይገኛል

ጸጋ እግዚአብሔር የት ይገኛል? በማንስ እጅ ይሰጣል? የእግዚአ ብሔር ጸጋ የሚታደልበት መንገዱ፥ የሚገኝበት ቤቱ በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ ከዚያም ውስጥ በሚካሄደው ሥርዓተ ጸሎትና በልዩ ልዩ ምሥጢራት አማካኝነት ጸጋ ይገኛል፡፡ ጸጋን የሚሰጥ እግዚአብሔር ቢሆንም ጸጋው የሚታደለው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በካህናት አማካኝነት ስለሆ ነ በመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያንን በመመሥረትና ምሥጢረ ክህነትን በማቋቋም ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጀምሮታል፡፡ የሥልጣነ ክህነት ምሳሌ የሆኑትን ም የመንግሥተ ሰማያትን ቁልፎች ለጴጥሮስና ለሐዋርያት ሰጥቷቸዋል፡፡ የመን ግሥተ ሰማያትንም ምሥጢር ለእነርሱ ገልጸላቸዋል (ማቴ.13÷11፤ 16÷19፤ 18÷18)፡፡ እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስ ከእናንተው ጋር ነኝ በማለት የሰጣቸው ተስፋ ከዛሬዎቹ ካህናት ጋር ክርስቶስ አብሮ የሚኖርና የሚሠራ መሆኑን የተስፋው ቃል ያስረዳናል (ማቴ.28÷20)፡፡

ቤተ ክርስቲያኑም የጸጋው ግምጃ ቤት የተባለችበትና የምሥጢራቱ ሁሉ መዝገብ የሆነችበት ምክንያት ምሥጢራት ሁሉ የሚገኙት ከዚያው መን ፈስ ቅዱስ ካለበት ከአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ብቻ በመሆኑ ነው፡፡ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ጸጋ አይሰጥም፥ መዳንም የለም፡፡ ነቢዩ ሕዝቅኤል በራእይ እንዳየው ከቤተ መቅደስ የሚወጣው ውኃ ወንዝ ሆኖ ሲፈስ የነካውን ነገር ሁሉ ይፈውሰውና ሕይወትም ይሰጠው እንደ ነበር ተጽፏል፡፡ "ሕያው ነፍስ ያለው ተንቀሳቃሽ ሁሉ ወንዙ በመጣበት ስፍራ ሁሉ በሕይወት ይኖራል፤ ይህም ውኃ በዚያ ስለ ደረሰ ዓሣዎች እጅግ ይበዛሉ፤ የባሕሩም ውኃ ይፈወሳ ል፥ ወንዙም በሚወጣበት ያለው ሁሉ በሕይወት ይኖራል" (ሕዝ.47÷1-12)፡፡ ይህም ከቤተ መቅደስ የሚወጣው ወንዝ ከቤተ ክርስቲያን ከሚገኘው ከመንፈስ ቅዱስ ሀብት እየተከፈለ የሚሰጠውን የጸጋ ምሥጢራት ያመለክታል፡፡ በተለይም በመስቀል ላይ ከክርስቶስ ጐን የፈሰሰው የሕይወት ውኃ አካሉ ከሆነችው ከቤተ ክርስቲያን በምሥጢረ ጥምቀት አማካኝነት ለዓለም ሁሉ የተሰጠው የሕይወት ጸጋ እንደሆነ እንረዳለን፡፡

www.eotc-mkidusan.org

የካህኑ ፍጹም አለመሆን የጸጋውን ሰጠታ አያግደውም

የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ አገልግሎት በሚያከናውኑት ካህናት አማካኝነት የእግዚአብሔር ጸጋ ለምእመናን እንደሚሰጥ ተምረናል፡፡ ነገር ግን በአኗኗራቸው ፍጹም ያልሆኑ አልፎ አልፎ አንዳንድ ካህናት ቢገኙ በምሥጢራቱ አፈጻጸምና በጸጋው አሰጣጥ ላይ ተጽእኖ ይኖረው ይሆንን? ለሚለው ጥያቄ መልሱ በካህናቱ ፍጹም ባለመሆን የተነሣ ጸጋ እግዚአብሔር ለምእመናን እንዳይደርስ ምንም የሚከለክለው ነገር የለም፡፡ ምክንያቱም የማይታየው ጸጋ ለምእመናን የሚሰጠው በመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን በመሆኑ ነው፡፡ በሙሴ ወንበር የተቀመጡት ፈሪሳውያን የሚያስተምሩትን ሕዝቡ እንዲቀበሉ ጌታ መፍቀዱና ክፉ ሥራቸውን ግን እንዳይከተሉ መከልከሉ ለተጠቀሰው ሁኔታ በምሳሌነት ያገለግላል (ማቴ.23፥1-3)፡፡ እንደ ገበሬ በመሆን ካህኑ ቃለ እግዚአብሔርን ይዘራል፤ በሰው ልቡና ውስጥ እንዲያድግ የሚያደርግ ግን እግዚአብሔር ነው፡፡

ስለዚሁ ጉዳይ ቅዱስ ጳውሎስ እንደሚከተለው ያስተምረናል፡፡ "እኔ ተከልሁ አጵሎስም አጠጣ ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር፡፡ እንግዲያስ የሚያሳድግ እግዚአብሔር እንጂ የሚተክል ቢሆን ወይም የሚያጠጣ ቢሆን አንዳች አይደለም" (1ኛቆሮ.3፥6-7)፡፡ ስለዚህ ምእመናን ይህን አውቀውና ተረድተው ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ከመሳተፍ ቸል እንዳይሉ ያስፈልጋል፡፡ ይልቁንስ ያለ ቅሬታ በሙሉ እምነትና በቅን ልቡና ሆነው ምእመናን ሁሉ ከነ ልጆቻቸውና ከነ ቤተሰቦቻቸው እግዚአብሔር በቸርነቱ ያዘጋጀላቸውን ጸጋ መንፈስ ቅዱስ በምስጋና እንዲቀበሉ ቤተ ክርስቲያን አደራ ትላለች፡፡

እንግዲህ ወሳኙ ነገር ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን የሚቀበሉ የምእመናን ልቡና በእምነትና በንሥሐ መዘጋጀቱ እንጂ የአቀባዩ ካህን በሁሉም ነገር ፍጹም አለመሆኑ የእግዚአብሔርን የጸጋ ስጦታ የማያግደው መሆኑን እንመን፡፡ ምክንያቱም በክርስቶስ የመጣልን ጸጋ የእግዚአብሔር የቁጣውና የፍርዱ መግለጫ ሳይሆን የምሕረቱና የይቅርታው መሣሪያ ሆኖ ለኃጢአተኞች ሁሉ የተሰጠ፥ በበደላችን የተነሣ ለቆሰለችውና ለታመመችው ነፍሳችን ፈውስ የሚያስገኝ እውነተኛ መድኃኒት ስለሆነ ነው፡፡ ስለዚህ ምንም ካህኑ የእግዚአብሔር መጋቢ ቢሆንም (ቲቶ 1፥7) ደኅንነታችን በእርሱ ጽድቅ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን በእግዚአብሔር ጸጋ አዳኝነት ላይ መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል፡፡

በዚሁ ጽሑፋችንን እናጠቃልላለን፡፡ በመጨረሻም ስሙን ያልገለጸው <u>የመዝገበ ሃይማኖት</u> ደራሲ በመጽሐፉ ፍጻሜ የጻፈውን በመጥቀስ የሚከተለውን ስብሐተ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር በመሆን እናቀርባለን፡፡

"ስብሐት ለእግዚአብሔር ወጣኒ ወፈጻሚ ከሃሊ ወገባሬ ኵሉ ለዓቱ ይደሉ አኰቴት እስከ ዘመነ ዘመናት በምድር ወበ ሰማያት በባሕር ወበቀላያት ለዓለመ ዓለም አሜን፡-
ለሚችል ለሚጀምር ለሚፈጽም ቻይ ሁሉን ለፈጠረ እግዚአ ብሔር ምስጋና ይድረሰው ለእሱ ከዘመን እስከ ዘመናት በምድርም በሰማይም በባሕርም በጥልቆችም ለዘለዓለሙ ምስጋና ይገባዋል አሜን፡፡"

"እመሂ ስሕትኩ አንትሙ እለ በመንፈስ አርትዕዎ፡ የተሳሳትኩትም ቢኖር እናንተ በመንፈስ ያላችሁ አቃኑት" [102]

አነግሥዶ ላስጀመረን፡ አስጀምሮ ላስፈጸመን ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይሁን፤ ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን፡፡[103]

---

[102] <u>መዝገበ ሃይማኖት</u>፤ በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የድርሰት ክፍል ተዘጋጀ (1959 ዓ.ም.) ገጽ 111፡፡

[103] "እግዚኦ ረስየነ ድልዋነ ከመ ንበል በአኰቴት አቡነ ዘበሰማያት"

www.eotc-mkidusan.org